# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የእግር ኳስ ስፖርትን ለመምራት እና ለማስፋፋት እያከናወነ ያለውን የአሰራር ሥርዓት በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት




መጋቢት 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

**ማውጫ** .................................................. I
**ክፍል አንድ** .................................................. 1
መግቢያ .................................................. 1
የፌዴሬሽኑ ራዕይ እና ተልዕኮ .................................................. 2
**ራዕይ (VISION)** .................................................. 2
የፌዴሬሽኑ ዓላማዎች .................................................. 2
**የፌዴሬሽኑ ስልጣንና ተግባር** .................................................. 3
የፌዴሬሽኑ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል .................................................. 4
**ድርጅታዊ መዋቅር** .................................................. 4
**የፌዴሬሽኑ የሰው ኃይል** .................................................. 5
የፌዴሬሽኑ የፋይናንስ ምንጭ .................................................. 5
የኦዲቱ ዓላማ .................................................. 6
ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ .................................................. 6
የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርት .................................................. 6
**የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት** .................................................. 7
ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ .................................................. 8
በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የሥራ ሂደት የሥራ ፍሰት መግለጫ (SYSTEM DESCRIPTION) .................................................. 9
**የቴክኒክና ልማት ስራ ሂደት የስራ ፍሰት** .................................................. 9
**የማህበረሰብ እግር ኳስ ልማትና ተሳትፎ በተመለከተ** .................................................. 9
**የሴቶች እግር ኳስ ልማት በተመለከተ:-** .................................................. 9
**የእግር ኳስ አሰልጣኞች ልማትን በተመለከተ:-** .................................................. 10
**የውድድር የስራ ሂደት ፍሰትን በተመለከተ፡** .................................................. 10
**ክፍል ሁለት** .................................................. 13
**የኦዲት ግኝቶች** .................................................. 13
2.1 የእግር ኳስ ስፖርትን በሀገር አቀፍ ደረጃ በማስፋፋት ብቁ እና ተተኪ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ለማፍራት የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን፣ የተዘረጋውም የአሠራር ሥርዓት አጥጋቢና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፣ .................................................. 13
**በስትራቴጂክ እቅድ የተገለጹ ተግባራት በአመታዊ እቅድ ተመንዝረው ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፣** .................................................. 13

ፌዴሬሽኑ ለፌደራል ስፖርት ኮሚሽን ዓመታዊ እቅድና ክንውን ሪፖርት መላኩን በተመለከተ ፥........................................................................14

የፌዴሬሽኑን አደረጃጀትን በተመለከተ፣ ..................................................15

የእግር ኳስ ስፖርትን ለሚያንቀሳቅሱ አካላት ስለሚደረገው ድጋፍና ክትትል በተመለከተ፣ ...........................................................................................16

በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተቀመጡ ግዴታዎች በፌዴሬሽኑ አባላት መተግበራቸውን በተመለከተ፣........................................................................17

በእግር ኳስ ስፖርት ዙሪያ የጥናትና የምርምር ሥራዎች መካሄዳቸውን በተመለከተ፣ ...18

የታዳጊ ወጣቶች ልማት ፕሮግራም የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር የሚጠይቀውን የፈቃድ አሰጣጥ ደንብ ስለማሟላታቸው፣...............................................................19

ክለቦች በአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር እና በአለም አቀፍ እግር ኳስ ማህበር የሚጠይቋቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላታቸውን እና ሂሳባቸውን ማስመርመራቸውን በተመለከተ፣.....20

በእግር ኳስ ስፖርቱ በሁሉም እድሜ ክልል ያሉ ሴቶች ተሳትፎን በተመለከተ፣...22

በህፃናት እግር ኳስ ልማት ዙሪያ የተዘጋጀው ሰነድ ፌዴሬሽኑና በባለድርሻ አካላት ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ ........................................................................22

ፌዴሬሽኑ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣........23

ፌዴሬሽኑ የሚያሰራቸውን የግንባታ ስራዎች በተመለከተ፣ ..................................24

2.2 በሀገሪቱ የእግር ኳስ ስፖርትን ለመምራትና ለማስተዳደር ቀልጣፋና ውጤታማ የሥልጠናና የውድድር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መሆኑን ማጣራት፣ ........................................................................................................................................................25

በፌዴሬሽኑ የሚሰጡ ስልጠናዎች የክልሎችንና የክለቦችን የስልጠና ፍላጎት ያገናዘበ ስለመሆኑ፣........................................................................................25

ለአሰልጣኞችና ለዳኞች መስፈርት ተዘጋጅቶ ደረጃ መሰጠቱን በተመለከተ፣...........26

የብሔራዊ ቡድን አሰልጣኞች መመልመያ መስፈርትን በተመለከተ፣......................27

በፕሮጀክቶች የታቀፉ ታዳጊ ሰልጣኞች በሥልጠና ወቅት ለሚያጋጥማቸው ጉዳት የህክምና አገልግሎት ስለመሰጠቱ፣ ....................................................................28

ፌዴሬሽኑ የሚያዘጋጃቸው የአገር አቀፍ ውድድሮች የአለም አቀፉን የእግር ኳስ ማህበር የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ፣...........................................................28

የፌዴሬሽኑ የተለያዩ ግንባታዎች አፈፃፀምን በተመለከተ ፣.................................29

የፀረ-ዶፒንግ /አበረታች መድሐኒቶች/ኮንቬንሽን ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ ....30

የሽልማት አሰጣጥ መመሪያን በተመለከተ፣................................................31

ብሔራዊ ቡድኑ የሚኖረውን የአቋም መለኪያ በተመለከተ፣ ..........................31

2.3 በፌዴሬሽኑ የእግር ኳስ ስፖርትን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ አጠባበቅ፣ አጠቃቀምና ልውውጥ አጥጋቢ እና አስተማማኝ መሆኑን መገምገም፣32

በፌዴሬሽኑ መረጃዎች ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የሚሆንበት ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፣ ...............................................................................................32

ክፍል ሶስት ....................................................................................................34

መደምደሚያ ....................................................................................................34

ክፍል አራት....................................................................................................36

የማሻሻያ ሃሳቦች ..............................................................................................36

አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (EVALUATIVE CRITERIA) .....................................42

አባሪ 3፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ ባለድርሻ አካላት ዝርዝር .............................................48

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የእግር ኳስ ጨዋታ ለመጀመሪያ ጊዜ በአገራችን የታወቀው በ1916 ዓ.ም ገደማ የውጭ አገር ማህበረሰብ አባላት ማለትም አርመኖች፣ ግሪኮች፣ እንግሊዞች፣ ህንድና ጣሊያኖች ቡድን አቋቁመው እርስ በርሳቸው ሲያደርጓቸው በነበሩት ውድድሮች አማካይነት ሲሆን፤ ስፖርቱ ወደ ትህምህርት ቤቶች የገባው በወቅቱ በዳግማዊ ሚኒሊክና በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ እንግሊዛዊያን መምህራን አማካይነት ነው፡፡ በዚህ መልክ የተጀመረው የእግር ኳስ ጨዋታ በትምህርት ቤቶች፣ በመኖሪያ አካባቢዎችና በሥራ ተቋማት መታወቅና መዘውተር ጀምሮ በመላ አገሪቱ በመስፋፋት ተወዳጅ ስፖርት ለመሆን በቅቷል፡፡

2. ኢትዮጵያዊያን የእግር ኳስ ክለቦች መቋቋም የጀመሩት ከ1928 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን፣ በጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አካባቢ የሚኖሩ የአራዳ ሰፈር ልጆች ያቋቋሙት የቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድን በክለቦች አደረጃጀት ታሪክ ቀዳሚነትን ይይዛል፡፡

3. በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች የስፖርቱ መታወቅና የእግር ኳስ ክለቦች መቋቋምን ተከትሎ ስፖርቱን በበላይነት የሚመራ አካል እንዲቋቋም ግፊት ማሳደሩን መነሻ በማድረግ የአገራችንን እግር ኳስ በበላይነት የሚመራ የስፖርት ጽ/ቤት በሚል ስያሜ የሚጠራ ጽ/ቤት በ1936 ዓ.ም በማስታወቂያ ሚኒስቴር ስር ተቋቋመ፡፡ በወቅቱ የነበረው ጽ/ቤት በአደረጃጀት፣ በሰው ኃይልና በፋይናንስ የተጠናከረ ባለመሆኑ ከእግር ኳሱ እንቅስቃሴ አንፃር የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ባለመቻሉ ጠንካራ የእግር ኳስ ተቋም ማቋቋም የወቅቱ ጥያቄ ሆኖ ጽ/ቤቱ በፌዴሬሽን ደረጃ እንዲቋቋም ተወሰነ፡፡ በዚህ መሰረት የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ በመውሰድ ክለቦች በተሳተፉበት ጠቅላላ ጉባኤ በፀደቀ መቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በ1941 ዓ.ም ተመሰረተ፡፡

4. ፌዴሬሽኑ በኢትዮጵያ ደረጃ የተቋቋመ ቢሆንም እንቅስቃሴው በአዲስ አበባ ብቻ የተወሰነ በመሆኑ ስያሜው ተቀይሮ የአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ተብሎ እስከ 1944 ዓ.ም ድረስ ዘለቀ፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ዓይነት ስያሜና አደረጃጀት

የኢትዮጵያን አግር ኳስ እድገት ለመከታተል አስቸጋሪ እንደሚሆን ስለታመነበት በ1944 ዓ.ም ፌዴሬሽኑ የቀድሞውን ስያሜና አደረጃጀት ማለት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የሚለው ስያሜ እንደያዘ ይገኛል፡፡

## የፌዴሬሽኑ ራዕይ እና ተልዕኮ

### ራዕይ (Vision)

5. የኢትዮጵያ እግር ኳስ ቀጣይነትና ሕዝባዊ መሠረት ያለው በማድረግ በአፍሪካ ከመጀመሪያዎቹ አራት ጠንካራ ሀገሮች ውስጥ አንዱ ሆኖ መገኘትና በዓለም አቀፍ መድረክ አህጉሪቱን የሚያስጠራ የእግር ኳስ ብሔራዊ ቡድን ማየት፣

### ተልዕኮ (Mission)

6. የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የእግር ኳስ መሰረተ ልማቶችን በማስፋፋት፣ በዘመናዊ ስልጠናና ውጤታማ ብሔራዊ አመራር በመስጠት የሀገሪቱን እግር ኳስ ስፖርት በሁሉም መስፈርት ማሳደግ፣ ማሻሻልና ማራኪ ማድረግ ነው፡፡ ፌዴሬሽኑ ግልፅነትና ተጠያቂነትን የባለድርሻዎች ፍላጎት ማርካትን ማዕከል ያደረገና የተቀናጀ አሰራርን በመዘርጋት በሀገሪቱ የእግር ኳስ ስፖርት ተወዳጅነት፣ ተመራጭነቱን፣ ትርፋማነቱና ብሔራዊ ሀብትነቱ ይበልጥ እያደገ እንዲሄድ ማድረግ የሚሉ ናቸው፡፡

## የፌዴሬሽኑ ዓላማዎች

7. የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን 2006 ዓ.ም በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡፡ እነሱም፡-

- የእግር ኳስ ስፖርትን በመላው አገሪቱ ማደራጀት፣ ማስፋፋት፣ ማሳደግ፣ መምራትና በውጤታማነት የህብረተሰቡን ፍላጎት ማርካት፣
- የልማት ፕሮጀክቶችን በመዘርጋት ወጣት ወንዶችና ሴቶች ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- የአገር ውስጥና ኢንተርናሽናል ውድድሮችን በማዘጋጀት ብሔራዊ ቡድኖች በቂ ሥልጠና እንዲያገኙና ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ፣

- ከተለያዩ አካላት ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር፣
- የዘር፣ የቀለም፣ የፖለቲካ፣ የሃይማኖት ወይም ማናቸውም ልዩነቶች ሳይደረጉ እግር ኳሱን መምራት እንዲሁም የአባላቱን መብትና ጥቅም እንዳይጓደል ማድረግ፣
- የአገራችንና ኢንተርናሽናል የስፖርት ፖሊሲዎችን፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲታወቁና እንዲከበሩ ማድረግ፣ የሚሉ ናቸው፡፡

## የፌዴሬሽኑ ስልጣንና ተግባር

8. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የስፖርት ኮሚሽን/ በአሁኑ ወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር/ ታህሳስ 2003 ዓ.ም የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን መመሪያ መሰረት በማድረግ ፌዴሬሽኑ መስከረም 2006 ዓ.ም ባዘጋጀው የመተዳደሪያ ደንብ ላይ የሚከተለው ስልጣንና ተግባር፡-

- ለመንግሥት ፖሊሲ፣ ሕግ፣ ደንብና መመሪያ ተገዢ መሆን፣
- ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ማቋቋምና ማስፋፋት፣
- የእግር ኳስ ስፖርትን የሚመለከቱ የተለያዩ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ማደራጀትና ማሰራጨት፣
- የአገር አቀፍና ኢንተርናሽናል ውድድሮችን ማካሄድ፣
- የእግር ኳስ ስፖርት ክለቦች እንዲደራጁ መመሪያ የማውጣትና ፈቃድ መስጠት፣
- የታዳጊ ወጣቶችንና የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ፣
- ምርጥ ስፖርተኞችን ለማፍራት የሚያስችል ዘመናዊ የምልመላና የሥልጠና ስልት መቀየስ፣
- ስፖርታዊ ጨዋነት እንዲሰፍን ለስፖርቱ አመራር፣ ለዳኞች፣ ለአሰልጣኞች፣ ለሐኪሞች፣ ለስፖርተኛውና ለደጋፊው የስፖርታዊ ጨዋነትን መርሆዎችና ሥነ-ምግባር ማስተማር፣ ስፖርታዊ ጨዋነቱ ተጥሶም ከተገኘ በደንባቸው መሠረት የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ማድረግ፣
- ከአለም አቀፍና ከአገር ውስጥ ተቋማት ጋር በመተባበር ኮርሶችን፣ ሴሚናሮችን፣ ወርክሾፖችንና ስልጠናዎችን ማዘጋጀትና ስራ ላይ ማዋል፣

- ስፖርቱን በሚመለከት የፌዴሬሽን ተወካዮች በአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስብሰባዎች መሳተፍና ውሳኔዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአሰልጣኞችን የዳኞችን የመመልመያ መስፈርትና ደረጃ ማውጣትና ፈቃድ መስጠት፣
- የሚመራውን ስፖርት በሚመለከት በሚቀርቡ ማናቸውም ክሶችና አቤቱታዎች ላይ ውሳኔ መስጠት፣
- አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልልም ሆነ በፌዴራል ስፖርቱ እንዲስፋፋና እንዲያድግ ድጋፍ ማድረግ፣
- ከመንግሥት ድጎማ ደረጃ በደረጃ የሚላቀቁበትና ራሳቸውን የሚችሉበት ስልት መቀየስና ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፣
- ለስፖርት ኮሚሽኑ ዓመታዊ ዕቅዱንና የየሩብ ዓመትና የዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ፣
- የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ የማውጣት፣ በጠቅላላ ጉባኤ የማጸደቅ እና ተግባራዊ የማድረግ፣
- ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን የፀረ-ዶፒንግ ኮንቬንሽን የማክበርና የማስከበር፣
- ማህበሩ በሚመራው ስፖርት በኢንተርናሽናልና በአገር አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ ውድድሮች ለሚሳተፉ አካላት ፈቃድ መስጠት፣
- በዓመት አንድ ጊዜ የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ፣
- ፌዴሬሽኖች የሚመሩት ስፖርት ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል እንዲዳረስ ጥረት ማድረግ፣
- ሌሎች ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ተግባራትን ማከናወን ያጠቃልላል፣

አሉት፡፡

## የፌዴሬሽኑ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

9. የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን 2006 ዓ.ም በጠቅላላ ጉባኤ በፀደቀው መቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተጠሪነቱ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲሆን ተደርጎ

ተቋቁሟል፡፡ ፌዴሬሽኑ በጠቅላላ ጉባዔ የሚመራ ሲሆን፣ በስሩ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ ኢመርጀንሲ ኮሚቴ፣ ዋና ፀሐፊ፣ ረዳት ዋና ፀሐፊ፣ አስተዳደርና ፋይናንስ፣ ማርኬቲንግ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት፣ እቅድ እና በጀት ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ደጋፊ የስራ ሂደቶች እንዲሁም የቴክኒክና ልማት፣ የውድድርና ማዘውተሪያ ስፍራዎች እና የኮሙኒኬሽን አብይ የስራ ሂደቶች ይገኛሉ፡፡ የፌዴሬሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

## የፌዴሬሽኑ የሰው ኃይል

10. ፌዴሬሽኑ በጥር ወር 2008 ዓ.ም 17 (31%) ሴት ሰራተኞች 37 (68%) ወንድ ሰራተኞች በድምሩ 54 የቋሚ ሰራተኞች ያሉ ሲሆን፣ በፌዴሬሽኑ ያለው የቋሚ ሰራተኞች የሰው ኃይል በሙያ ሲተነተን ሁለተኛ ዲግሪ 5 (9%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ 9 (16%)፣ ዲፕሎማ 10 (18%) ሠርተፊኬትና እና ከዛ በታች ያሉ 30 (55%) ነው፡፡

## የፌዴሬሽኑ የፋይናንስ ምንጭ

11. ፌዴሬሽኑ በመቋቋሚያ ደንቡ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት ከሚመደብለት በጀት እና ከእርዳታ፣ ከማርኬቲንግ፣ ከስፖንሰርሺፕ፣ ከስታዲየም ቲኬት ሽያጭ እና ሌሎች ገቢ የሚያገኝ ሲሆን ከ2005-2008 ሩብ ዓመት ድረስ የተመደበለት በጀትና ያገኘው እርዳታ እንዲሁም የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | ከመደበኛ በጀት | | | ከዕርዳታ፣ ከማርኬቲንግ፣ ከስፖንሰርሺፕ፣ ከስታዲየም ቲኬት ሽያጭ እና ሌሎች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ስራ ላይ የዋለ | | | ስራ ላይ የዋለ | |
| | የተፈቀደ | በብር | በ% | የተሰጠ | በብር | በ% |
| 2005 | 9,380,000 | 8,490,000 | 91% | 75,169,948 | 57,501,487 | 77 % |
| 2006 | 1,791,300 | 1,620,380 | 90% | 79,236,143 | 70,473,209 | 89% |
| 2007 | 2,612,019 | 2,612,019 | 100 % | 62,051,663 | 60,507,710 | 98% |
| 2008 ግማሽ ዓመት | 40,000,000 | 24,500,000 | 61% | 20,000,000 | 16,540,000 | 83% |

## የኦዲቱ ዓላማ

12. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በእግር ኳስ ፌዴሬሽን የእግር ኳስ ስፖርትን በማስፋፋት ብቃት ያላቸው ስፖርተኞችን ለማፍራት ያለው የአሰራር ስርዓት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን እንዲሁም በባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር ማድረጉን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል ብሎም ለማስወገድ የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ

13. “ፌዴሬሽኑ የአገሪቱን የእግር ኳስ ስፖርት ለመምራት እና ለማስፋፋት የሚያግዝ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም” የሚል ነው፡፡

## የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርት

### የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች

14. ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተለይተዋል፡፡ እነርሱም፡-

1 የእግር ኳስ ስፖርትን በሀገር አቀፍ ደረጃ በማስፋፋት ብቁ እና ተተኪ የእግር ኳስ ተጫዋች ለማፍራት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን እና የተዘረጋውም የአሠራር ሥርዓት አጥጋቢና ውጤታማ መሆኑን ማጣራት፣

2 በሀገሪቱ የእግር ኳስ ስፖርትን ለመምራትና ለማስተዳደር ቀልጣፋና ውጤታማ የሥልጠናና የውድድር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መሆኑን ማጣራት፣

3 በፌዴሬሽኑ የእግር ኳስ ስፖርትን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ፣ አጠባበቅ፣ አጠቃቀምና ልውውጥ አጥጋቢ እና አስተማማኝ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት

15. ከላይ የተለዩትን ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 44 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን መቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ፣ የፌዴሬሽኑ ከ2005-07 ድረስ ያሉ እቅድና የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የፌዴሬሽኑ ከ2001-05 እና ከ2006-2011 ድረስ ያሉ ስትራቴጂክ እቅዶች፣ የፌዴሬሽኑ የማኔጅመንትና የስራ አስኪያጅ ቃለ-ጉባኤ፣ የፌዴሬሽኑ የአደረጃጀት ጥናት፣ የፌዴሬሽኑ የBPR ጥናት፣ የፊፋ ስታተስ ፣ የተጫዋቾች ደረጃና ዝውውር መመሪያ፣ በህፃናት እግር ኳስ ልማት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ የስምምነት ሰነድ፣ የካፍ ፈቃድ አሰጣጥ ደንብ እና በስፖርት ኮሚሽን የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የተዘጋጁትም መመዘኛ መስፈርቶች ለፌዴሬሽኑ ተልከው አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶች በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

## ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

16. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2005 እስከ 2008 የመጀመሪያው ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ያሉትን የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

17. ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ሲሆን በተጨማሪም ከፌዴሬሽኑ ጋር በቅርበት በሚሰሩትና በናሙና ከተመረጡት በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የስፖርት ኮሚሽኖች፣ የእግር ኳስ ፌዴሬሽኖች እንዲሁም በሁለቱም ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ከሚገኙ በናሙና በተመረጡ ስድስት ክለቦች፣ ከአስራ አምስት ዓመት በታችና በህፃናት ዙሪያ ከሚሰሩ ፕሮጀክቶች አስራ ሁለት እና ከፌዴሬሽኑ ጋር በታዳጊ ሕፃናት ልማት ፕሮጀክት ስምምነት ሰነድ ካዘጋጁት ባለድርሻ አካላት (ወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር፣ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን) ውስጥ በናሙና ለተመረጡት ወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እና ትምህርት ሚኒስቴር በመገኘት ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ማስረጃዎችን በመከለስ ነው፡፡ በኦዲቱ ወቅት የታዩ ባለድርሻ አካላት ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

# በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የሥራ ሂደት የሥራ ፍሰት መግለጫ
(System Description)

## የቴክኒክና ልማት ስራ ሂደት የስራ ፍሰት

18. በእግር ኳስ ፌዴሬሽን ስር የቴክኒክና ልማት ስራ ሂደት የስራ ፍሰት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ማለትም የማህበረሰብ እግር ኳስ ልማትና ተሳትፎ፣ የሴቶች እግር ኳስ ልማት እና የእግር ኳስ የአሰልጣኞች ልማት በመባል ይከፈላሉ፡፡

## የማህበረሰብ እግር ኳስ ልማትና ተሳትፎ በተመለከተ

19. የህብረተሰቡን የእግር ኳስ የተሳትፎ ፍላጎት የመለየቱ ተግባር በሁለት ዘርፍ የሚተገበር ሲሆን፣ አንደኛው የክለቦች እግር ኳስ አቀፍ ማህበራዊ ልማት ሰነድ በማዘጋጀት የጋራ የውይይት መድረክ በመፍጠር አስፈፃሚ አካላትን በማሳተፍ ሳምፕል ፕሮጀክት በማዘጋጀት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ግንዛቤ መፍጠር ሲሆን ፣ ሁለተኛው ዘርፍ የህፃናትና ታዳጊ ወጣቶች እግር ኳስ ልማት ሰነድ በማዘጋጀት የህፃናት እግር ኳስ ማስፋፊያ የመግባቢያ ሰነድ እንዲዘጋጅ በማድረግ ከባለድርሻ የሚኒስቴር መ/ቤቶች ጋር ሰነድ የሚፈራረም ሲሆን በተጨማሪም የእግር ኳስ አልሚዎችን ሰነድ በማዘጋጀት ከአልሚዎች የጋራ የግንዛቤና የውይይት መድረክ በመፍጠር ከአህጉራዊና ዓለም አቀፍዊ የእግር ኳስ ማህበራት ጋር ግንኙነትን በማጠናከር የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎችን በመንደፍና ደጋፊ የማስልጠኛ ማንዋሎችን በማዘጋጀት ወደ ትግበራ በመግባት የቁጥጥር፣የግምገማና የግብረ- መልስ ስርዓት ይፈጥራል፡፡

## የሴቶች እግር ኳስ ልማት በተመለከተ:-

20. የሴቶች እግር ኳስ ልማት ተግባር ሁለት ምድቦችን የሚያከናውን ሲሆን አንደኛው የሴቶችን እግር ኳስ የተሳትፎ ፍላጎት በመለየት የሴቶችን እግር ኳስ ልማት ፓኬጅ እና የማስፈፀሚያ ሰነዶችና ደጋፊ ማንዋሎችን በማዘጋጀት በፓኬጁ ላይ ከባለድርሻና ተባባሪ አካላት ጋር በመወያየት የደጋፊ አደረጃጀትን በመፍጠር በፍላጎታቸው ዙሪያ ሙያዊ ስልጠናዎችን በማዘጋጀትና በማብቃት በየተሳትፎ አይነትና በየዕድሜ ደረጃ ያሉ ሴቶች ተጠቃሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የቁጥጥር ፣ግምገማና የግብረ- መልስ

ስርዓት መፍጠር ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል ከአህጉራዊና አለም አቀፋዊ የእግር ኳስ ማህበራት ጋር ግንኙነቶችን በማጠናከር ሙያዊ፣ ቴክኒካዊና ቁሳዊ ድጋፎችን በማስተባበር የተደራጁ ሴቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ በማመቻቸት በእግር ኳስ መስኩ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶችና ወጣት ልጃገረዶችን የማፍራትና የማብቃት ተግባርን ያከናውናል፡፡

## የእግር ኳስ አሰልጣኞች ልማትን በተመለከተ፡-

21. በሶስት ክፍሎች የሚያሳትፍ ሲሆን የመጀመሪያው በእግር ኳስ አሰልጣኖች የልማት ፓኬጅ በማዘጋጀት የማሰልጠን ፍቃድ ማስፈጸሚያ ስነድ ፣ የክለብ ማሰልጠኛ መመሪያ ፣ የግብ ጠባቂዎች አሰልጣኞች ማሰልጠኛ ፓኬጅ እና የተጠባባቂ ብሄራዊ ቡድኖች ማቋቋሚያ ሰነድ ያዘጋጃል፡፡ በሁለተኛው የልማት ፓኬጅ የኢንስትራክተሮችና የአሰልጣኞች ስልጠና ደረጃ ዕድገትና ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓት በመዘርጋት የብሄራዊ ቡድኖች አሰልጣኞች ፎርም ማቋቋሚያ ሰነድ ያዘጋጃል፡፡ የፉት ሳልና ቢች ፉት ቦል የአሰልጣኞችን ስልጠናዎች ያመቻቻል፣በፓኬጅ ላይ ከባለድርሻና ተባባሪ አካላት ጋር በመወያት ደጋፊ አደረጃጀትን መፍጠር፣ የማስፈፀሚያ ሰነዶችንና ደጋፊ ማንዋሎችን አዘጋጅቶ በየፍላጎታቸው ዙሪያ ሙያዊ ስልጠናዎችን ማዘጋጀትና ማብቃት በዚህም መሰረት የቁጥጥር፣ የግምገማና የግብረ-መልስ ስርዓት ይፈጥራል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ ከአህጉራዊና አለም አቀፋዊ የእግር ኳስ ማህበራት ጋር ግንኙነት በማጠናከር ሙያዊ፣ ቴክኒካዊና ቁሳዊ ድጋፎችን ያስተባብራል፡፡ የክልል ፌደሬሽኖችና የተደራጁ ክለቦች አሰልጣኞች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡ በመጨረሻም እግር ኳሱን ሙያዊ በሆነ አስለጣጠን ማስፋፋትና ማሳደግ የሚችሉ ኢንስተራክተሮችና አሰልጣኞችን በብዛትና በጥራት ያበቃል፡፡

## የውድድር የስራ ሂደት ፍሰትን በተመለከተ፡

22. በእግር ኳስ ፌዴሬሽን ስር ያሉ የውድድር የስራ ሂደቶች በሁለት ዋና ዋና የውድድር ሂደቶች ማለትም የሀገር ውስጥ እና የኢንተርናሽናል የውድድር ሂደት በመባል ይከፈላሉ፡፡

## ሀ/ የሀገር ውስጥ የውድድር ሂደት

23. ይህ የውድድር ሂደት ሶስት ንዑስ የስራ ሂደቶችን (የውድድር የስራ ሂደት፣ የውድድር የስራ ሂደት ፀሐፊ እና የብሔራዊ ሊግ ውድድሮች ጸሐፊ) ያጠቃልላል፡፡

### 1. የውድድር የስራ ሂደት

በዚህ ሂደት ውስጥ ከስፖርት ክለቦች፣ ከሙያ ማህበራት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በጋራ በመሆን ለስፖርት ክለቦች፣ ለዩኒቨርሲቲዎች፣ ለሴቶችና ወጣቶች የተለያዩ ውድድሮችን በማዘጋጀትና በማሳተፍ ለአገር፣ ለአህጉር እና ለአለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሚሆኑ የእግር ኳስ ተጫዋቾችን ማፍራት፣ የክለቦች አደረጃጀት ደንብ የማውጣት፣ ክለቦችን በደንብ መሰረት እንዲመዘገቡ የማድረግ ተግባራትን ይከናወናል፡፡

### 2. የውድድር የሥራ ሂደት ፀሐፊ

የውድድር የሥራ ሂደት ፀሐፊ ከሊግ ኮሚቴ፣ ከብሔራዊ ሊግ፣ ከዲሲፕሊን ኮሚቴና ከይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ጋር በመሆን የተለያዩ የወንዶች፣ የሴቶችና የወጣቶች ፕሪሚየር ሊግ ውድድር ያካሂዳል፣ የውድድር ደንብ ማንዋል ያዘጋጃል፡፡

### 3. የብሄራዊ ሊግ ውድድሮች ፀሀፊ

የብሄራዊ ሊግ ውድድሮች ፀሀፊ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከፌደራል ስፖርት ኮሚሽን፣ ከትምህርት ሚኒስቴር እና ከፖሊስ ጋር በመተባበር የውድድር ሪከርዶችን፣ ውጤቶችን በመመዝገብ መረጃ ይይዛል፣ የመወዳደሪያ ስፍራዎችና መሳሪያዎች ያዘጋጃል፣ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከከፌደራል ስፖርት ኮሚሽን፣ትምህርት ሚኒስቴር እና ከፖሊስ ጋር በጋራ በመሆን ሀገር አቀፍ የስፖርት ፌስቲቫሎች በማዘጋጀትና የመምረጥ ስራ ያከናውናል፣ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከፌደራል ስፖርት ፖሊስ ጋር በመሆን የመላው ኢትዮጵያ ጨዋታዎች ውድድር የማዘጋጀትና የማሳተፍ ተግባር ያከናውናል፣ ከፌደራል ስፖርት ኮሚሽን ጋር በመሆን መላው አፍሪካ ጨዋታዎች ያሳትፋል፣ ምርጥ ስፖርተኞችን ለኢንተርናሽናል ውድድር ይመርጣል እና በተለያዩ ውድድሮች አሸናፊ ስፖርተኞችንና ክለቦች ሽልማት ይሰጣል፡፡

## ለ.የኢንተርናሽናል ውድድር ሂደት

24. ይህ የውድድር ሂደት የብሄራዊ ቡድን ተጨዋቾችን በየደረጃው በመምረጥ ያዘጋጃል፣ የCAF የክለቦች ሻምፒዮና ውድድር ያካሂዳል፣ የCAF ኮንፌደሬሽን ክለቦች ውድድር ያሳትፋል፣ የአፍሪካ ዋንጫ (የCAF) ውድድር ይሳተፋል፣ የአለም ዋንጫ (የFIFA) ውድድር ላይ ይሳተፋል፣ በአህጉርና በአለም አቀፍ ውድድር ሀገሪቱን የሚወክሉ ምርጥ ስፖርተኞችን በማፍራት ሻምፒዮና የመሆንና የመሳሰሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

## 2.1 የእግር ኳስ ስፖርትን በሀገር አቀፍ ደረጃ በማስፋፋት ብቁ እና ተተኪ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ለማፍራት የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን፣ የተዘረጋውም የአሠራር ሥርዓት አጥጋቢና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፣

**በስትራቴጂክ እቅድ የተገለጹ ተግባራት በአመታዊ እቅድ ተመንዝረው ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፣**

25. ፌዴሬሽኑ የስትራቴጂክ ዕቅድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ በስትራቴጂክ ዕቅድ ያቀዳቸውን ተግባራት በዓመት እና በሩብ አመት ዕቅድ በማካተት አቅዶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ በተዘጋጀውም ዕቅድ መሰረት በየሩብ ዓመት እና በየአመቱ አፈጻጸሙን በመገምገም ክፍተቶችን እና የተወሰዱ የመፍትሂ እርምጃዎችን በሚያዘጋጀው የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ውስጥ እንዲካተቱ ሊያደርግ ይገባል፡፡

26. ይሁን እንጂ ፌዴሬሽኑ በስትራቴጂክ እቅድ ላይ የተገለፁ ተግባራትን ሁሉ ወደ አመታዊ እቅድ መንዝሮ ያልሰራ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ ለዚህም እንደማሳያ የሚሆነው ከ2001-05 ባለው ስትራቴጂክ እቅዱ ላይ የሀገር ውስጥ ውድድሮች በዞን፣ በወረዳ፣ በቀበሌና በትምህርት ቤቶች፣ የክለብ ታዳጊዎች ሻምፒዮናና አዲስ ውድድር ዓይነት የመፍጠር ስራዎችን፣ የኢንተርናሽናል ውድድሮች በምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ፣ ለቤጂንግ ኦሎምፒክ ማጣሪያ /በወንድና በሴት/፣ ኢንተርናሽናል የወዳጅነት ጨዋታዎች ማድረግን እና የስፖርት ህክምና ስልጠና መስጠትን ቢያቅድም እስከ 2005 ዓ.ም ዓመታዊ እቅድ ውስጥ አለማካተቱ፣ የየዓመት የእቅድ አፈፃፀሙን በወር፣ በየሩብ ዓመትና በአመቱ መጨረሻ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እየቀረበ የማይገመገም መሆኑ እንዲሁም ከ2006 ዓ.ም በስተቀር በሌሎች አመታት የእቅድ ክንውን ሪፖርቱ ውስጥ አፈፃፀም ላይ የታዩ ክፍተቶችን እና የተወሰዱ የመፍትሂ እርምጃዎችን የማያካትት መሆኑ ታውቋል፡፡

27. ስለሁኔታው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ በስትራቴጂክ ዕቅዱ ላይ ያሉ ሁሉም ተግባራት ወደ አመታዊ ዕቅድ ተመንዝረው ተግባራዊ አለመደረጋቸውን፣ ፌዴሬሽኑ በደራሽ ስራዎች ላይ የተጠመደ በመሆኑ ወቅቱን ጠብቆ ግምገማ የማያደርግ መሆኑን እና በአፈፃፀም ሪፖርት ላይ የታዩ ክፍተቶችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ማካተትን በተመለከተ ለእቅድ ዝግጅቱ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ባለመቻሉ የተከሰተ ችግር መሆኑን በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) በሰጡት አስተያየት ላይ ገልጸዋል፡፡

28. ፌዴሬሽኑ በስትራቴጂክ እቅድ የተቀመጡ ተግባራትን ወደ አመታዊ እቅድ በመከፋፈል እየተመነዘረ እንዲተገበሩ አለማድረጉ፣ ዕቅድ አፈጻጸምን በየሩብ ዓመትና በዓመቱ መጨረሻ ላይ አለመገምገሙ እና በአፈፃፀሙ ዙሪያ ያሉ ችግሮችን ከነመፍትሄ ሃሳቦች አለማስቀመጡ የተለያዩ ተግባራት በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዳይከናወኑ እንዲሁም መፍትሄ የሚያስፈልጋቸውን ችግሮች በወቅቱ እርምጃ እንዳይወሰድባቸው ከማድረጉም በላይ በስትራቴጂክ ዕቅዱ ዘመን ካስቀመጠው አላማና ግብ እንዳይደርስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ፌዴሬሽኑ ለፌደራል ስፖርት ኮሚሽን ዓመታዊ እቅድና ክንውን ሪፖርት መላኩን በተመለከተ ፡

29. ፌዴሬሽኑ ለፌደራል ስፖርት ኮሚሽን ዓመታዊ እቅዱንና የየሩብ ዓመትና የዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

30. ይሁን እንጂ ፌዴሬሽኑ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የየሩብ የግማሽ ዓመት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለፌደራል ስፖርት ኮሚሽን የማይልክ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

31. ስለሁኔታው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለኮሚሽኑ ለመላክ አደረጃጀቱ የማይፈቅድ በመሆኑ የማይልክ መሆኑን በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት የገለፁ ሲሆን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሚልኩ ቢገልፁም ማስረጃው አልቀረበም፡፡

32. ኃላፊዎቹ ይሁን ይበሉ እንጂ የፌዴሬሽኑ የመተዳደሪያ ደንብ ላይ በግልፅ የተቀመጠ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

33. ፌዴሬሽኑ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በየጊዜው የየሩብ ዓመቱን እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት አለመላኩ የሚመለከተው አካል ያሉበትን ችግሮች በመለየት በየጊዜው የመፍትሄ ሃሳብ እንዳይሰጠው እንዲሁም እንደማህበር አገሪቱ ውስጥ ለመንቀሳቀስ የገባውን ግዴታ እንዳይወጣ ያደርገዋል፡፡

### የፌዴሬሽኑን አደረጃጀትን በተመለከተ፣

34. የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዳ አደረጃጀት ሊኖረው እና በአደረጃጀቱም የውስጥ ኦዲት ክፍልን ሊያካትት ይገባል፡፡

35. ይሁን እንጂ ፌዴሬሽኑ ከ 2006-11 ባለው ስትራቴጂክ እቅድ ላይ የአለም አቀፍ የአደረጃጀት መነሻ ያደረገ መዋቅር አዘጋጅቶ ተግባራዊ ለማድረግ አቅዶ በ2006 ዓ.ም የውስጥ መዋቅራዊ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ፍላጎት ጥናት ያስጠና ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፡፡ እግር ኳሱን ሊመራ የሚችል አደረጃጀት እና የተሟላ የሰው ኃይል የሌለ መሆኑ፣ እንዲሁም አሁን በስራ ላይ ባለውም ሆነ አዲስ ባስጠናው አደረጃጀት ላይ የውስጥ ኦዲትን ያላካተተ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

36. ስለሁኔታው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ ከላይ የተጠቀሰው ጉዳይ ትክክል መሆኑን እንደሚያምኑበትና የፌዴሬሽኑ የፋይናንስ አቅም ማነስ (ቋሚ የገንዘብ ምንጭ አለመኖር) እና የኮሚቴው አባላት በነዚህ ችግሮች ላይ ተወያይቶ ችግሩን ለመፍታት ጊዜ ሰጥተው እየሰሩ ባለመሆኑ የተከሰተ ችግር መሆኑን፣ የውስጥ ኦዲት ክፍል መኖሩ እስካሁን በፌዴሬሽኑ ስላልታመነበት እንደሆነና ለወደፊት ግን የፋይናንስ አቅሙ እየጨመረ በመምጣቱ እየተከለሰ ባለው የአደረጃጀት ጥናት ላይ እንዲካተት እንደሚደረግ እንደ አጠቃላይ ግን የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅም ውስንነት በመኖሩ የአደረጃጀት ጥናቱ ተግባራዊ ሊሆን እንዳልቻለ በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ለተላከላቸው ረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ ደግሞ በአዲሱ የፌዴሬሽኑ የአደረጃጀት የክለሳ ጥናት ተፈላጊ የስራ መደቦችን ከኦዲት ጋር በማካተት ተዘጋጅቶ የመጨረሻው የአፈጻጸም ምዕራፍ ላይ እንደሚገኝ ገልጸው አስተዳደራዊ መዋቅሩን እና የስራ መደቦችን ማሻሻያ ዝርዝር ሰነድ አያይዘው

ቢያቀርቡም በሚመለከተው አካል ቀርቦ ስለመፅደቁ መረጃው ባለመቅረቡ የተከለሰ መዋቅር ስለመሆኑ መቀበል ያዳግታል፡፡

37. ፌዴሬሽኑ ያለውን የአደረጃጀት ጥናት በወቅቱ ተግባራዊ እንዲሆን አለማድረጉ ለህብረተሰቡ/ለባለድርሻ አካላት በእግር ኳስ ስፖርት ዙሪያ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ተደራሽ እንዳይሆን የሚያደርገው በመሆኑ አገሪቱ በስፖርቱ ማግኘት ያለባትን ጥቅሞች እንዳታገኝ እና ደካማ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በመፍጠር የፌዴሬሽኑን ሀብት ለብክነትና ለህገወጥ አሰራር በር ይከፍታል።

## የእግር ኳስ ስፖርትን ለሚያንቀሳቅሱ አካላት ስለሚደረገው ድጋፍና ክትትል በተመለከተ፣

38. ፌዴሬሽኑ በሁሉም ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች የእግር ኳስ ስፖርትን በኃላፊነት የሚያንቀሳቅሱ አካላት እንዲቋቋሙና እንዲደራጁ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

39. ፌዴሬሽኑ በሁሉም ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ እግር ኳስ ፌዴሬሽኖች፣ ክለቦችና ፕሮጀክቶች እንዲቋቋሙና እንዲደራጁ ድጋፍና ክትትል ያላደረገ መሆኑ፣ በ2007 ዓ.ም 11 የክልል ፌዴሬሽኖችን አደረጃጀት በማሻሻል ለእግር ኳሱ ዕድገት እንዲያበረክቱ የማስፈጸም አቅማቸውን ለመገንባት የታቀደ ቢሆንም ያልተከናወነ መሆኑ፣ በየደረጃው የሚገኙ የፕሪሚየርና የብሔራዊ ሊግ ክለቦች አደረጃጀት እንዲሻሻልና የማስፈጸም አቅማቸውም እንዲገነባ ማድረግን እና የክለብ ፈቃድ አሰጣጥ (licensing) ሥርዓትን እንደሚዘረጋ ቢታቀድም ያተከናወነ መሆኑ፣ የክልል እግር ኳስ ፌዴሬሽኖችና ክለቦች ወጥ የሆነ መዋቅራዊ አደረጃጀት እንደሌላቸው እና በቀድሞ ስፖርት ኮሚሽን ሐምሌ 2004 ዓ.ም የስፖርት ክለቦች ያለባቸውን የአደረጃጀት ችግር ለመፍታት የአደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት ማንዋል ያስጠና ቢሆንም ፌዴሬሽኑ በክለቦች ላይ ተግባራዊ እንዲሆን አለማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

40. ስለሁኔታው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ ፌዴሬሽኑ እነዚህን ተግባራት በፋይናንስ አቅም ማነስ የተነሳ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ አለመቻሉን በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በቀድሞ ስፖርት ኮሚሽን የተጠናው

የአደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት ማንዋል ተግባራዊ ያልሆነበትን ምክንያት ላይ አስተያየት እንዲሰጡ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው ጥናቱ በአገሪቱ በሁሉም ፌዴሬሽኖች ተግባራዊ መደረግ ያለበት ስለሆነ የእግር ኳስ ፌዴሬሽኑ የአደረጃጀት ጥናቱን ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

41. ፌዴሬሽኑ በሁሉም ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች እየተከናወኑ ያሉ የእግር ኳስ ፕሮጀክቶች እና እንቅስቃሴዎችን በመከታተል ያሉባቸውን ክፍተቶች እየለየ የማይደግፍ ከሆነ የአገሪቱ እግር ኳስ እድገት ወደ ተሻለ ደረጃ እንዳይደርስ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

## በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተቀመጡ ግዴታዎች በፌዴሬሽኑ አባላት መተግበራቸውን በተመለከተ፣

42. ፌዴሬሽኑ በመተዳደሪያ ደንብ ላይ የተቀመጡ ግዴታዎች (ማንኛውንም የአለምአቀፉን (FIFA)፣ የአህጉር አቀፉን (CAF) እና የክፍለ አህጉራቱን (CECAFA) ስፖርት ማህበራት ደንብ፣ መመሪያና ውሳኔዎች የማክበርና የማስከበር፣ የአለም አቀፉ የእግር ኳስ ማህበር ቦርድ (IFAB) የተወሰኑትን የጨዋታ ህጎች የማክበርና የመተዳደሪያ ደንቡ በአባላት መከበሩን ማረጋገጥ ወዘተ) አባላቱ መወጣታቸውን የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

43. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ፌዴሬሽኑ በመተዳደሪያ ደንብ ላይ የተቀመጡ የአባላት ግዴታዎች ሁሉ አባላቱ (የክልል ፌዴሬሽኖች፣ ክለቦች ወዘተ) እየተወጡ ስለመሆኑ የሚከታተልበት ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ ለዚህም እንደማሳያ የሚሆነው በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት ክለቦች (ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ የኢትዮጵያ ቡና፣ ቡራዩ ከተማ፣ ሰበታ ከተማ፣ መቀሌ ከተማ እና ወልዋሎ) ከአባልነት ግዴታዎች ውስጥ ዓመታዊ የአባልነት ክፍያ ብቻ የሚፈፅሙ መሆኑን፣ የክልል እግር ኳስ ፌዴሬሽኖች ግዴታዎቻቸውን ስለመፈፀማቸው ክትትል የማይደረግ መሆኑ ታውቋል፡፡

44. ስለሁኔታው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ የክልል እግር ኳስ ፌዴሬሽኖችን በተመለከተ በዓመት አንድ ጊዜ በሚዘጋጀው ጠቅላላ ጉባኤ መገኘታቸውን እንደ ክትትል እንደሚቆጥሩት፣ ክለቦችን በተመለከተ ሌሎች ግዴታዎችን ባይወጡም ዓመታዊ የአባልነት ክፍያቸውን ሲፈፅሙ እንደ ክትትል

እንደሚቆጥሩት በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

45. ይሁን እንጂ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተቀመጡት የአባልነት ግዴታዎች የተጠቀሱት ተግባራት ብቻ አለመሆናቸውን (ማንኛውንም (የአለምአቀፉን (FIFA)፣ የአህጉር አቀፉን (CAF) እና የክፍለ አህጉራቱን (CECAFA) ስፖርት ማህበራት ደንብ፣ መመሪያና ውሳኔዎች የማክበርና የማስከበር፣ የአለም አቀፉ የእግር ኳስ ማህበር ቦርድ (IFAB) የተወሰኑትን የጨዋታ ህጎች የማክበርና የመተዳደሪያ ደንቡ በአባላት መከበሩን ማረጋገጥ ወዘተ ስለሆነ ክትትል እያደረግን ነው ተብሎ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

46. ፌዴሬሽኑ አባላት በመተዳደሪያ ደንቡ የተቀመጡ ግዴታዎችን ሁሉ ስለመፈፀማቸው ክትትል አለማድረጉ ዘመናዊ የእግር ኳስ ስፖርትን በተገቢው ህግና ሥርዓት ሳይሆን ስፖርቱ በዘፈቀደ እንዲመራ ያደርገዋል፡፡

## በእግር ኳስ ስፖርት ዙሪያ የጥናትና የምርምር ሥራዎች መካሄዳቸውን በተመለከተ፣

47. ፌዴሬሽኑ በእግር ኳስ ስፖርት ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በራሱም እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊያካሂድና ሲጸድቁም ተግባራዊ ሊያደርጋቸው ይገባል፡፡ የሚጠኑት ጥናቶችም የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት ያስገኙት ፋይዳ፣ በየትምህርት ቤት የእግር ኳስ ሁኔታ፣ የብሔራዊ ቡድኖቹ ውጤት፣ የወደፊቱ የአገሪቱ የእግር ኳስ የመሳሰሉት ላይ ሊሆን ይገባል፡፡

48. ፌዴሬሽኑ በእግር ኳስ ስፖርት ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በማከናወን አፀድቆ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ ያለበት ቢሆንም በየዓመቱ የሚሰራቸውን ጥናቶች ብዛት በእቅድ በመያዝ አለማከናወኑ ታውቋል፡፡

49. ስለሁኔታው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በነበራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጠው ምላሽ የከፍተኛ ዲቪዚዮን /supper league/ ውድድር መመሪያ ከመዘጋጀቱ በፊት ጥናት በማካሄድ በጥናቱ መሰረት መመሪያው መዘጋጀቱን ቢገልጹም ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ ከሰጡት ምላሽ ጋር ጥናት ተጠንቷል በማለት አያይዘው ያቀረቡት ሰነድ ለ 2008 ዓ.ም የቡድኖች አደረጃጀት መነሻ የቀረበ የውሳኔ ሃሳብ እንጂ የተጠና ጥናት ባለመሆኑ የሰጡትን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

50. ፌዴሬሽኑ በእግር ኳስ ስፖርት ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በማከናወን አፀድቆ ተግባራዊ እንዲሆኑ አለማድረጉ ስፖርቱ በሳይንሳዊ ጥናቶች ተደግፎ ከነበሩበት ችግሮች በመላቀቅ ወደ ተሻለ ደረጃ እንዳይደርስ ያደርጋል፡፡

### የታዳጊ ወጣቶች ልማት ፕሮግራም የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር የሚጠይቀውን የፈቃድ አሰጣጥ ደንብ ስለማሟላታቸው፣

51. ፌዴሬሽኑ የታዳጊ ወጣቶች ልማት ፕሮግራም ለማቋቋም ፍቃድ የሚጠይቁ አካላት በአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር የፈቃድ አሰጣጥ ደንብ ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ፈቃድ ተሰጣቸውን አካላት በየዓመቱ ክትትልና ግምገማ በማድረግ የግብረ መልስ ሪፖርት የሚላክበትን ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል::

52. የታዳጊ ወጣቶች ልማት ፕሮግራሞች የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር የፈቃድ አሰጣጥ ደንብ ላይ ፕሮጀክቶቹ (የሰው ሀይል፣ የስልጠናና የውድድር አቅርቦት፣ የፋይናንስ ምንጭ፣ የተጫዋቾች ህክምና አቅርቦት ወዘተ) ማሟላት እንዳለባቸው ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ትግራይና ኦሮሚያ ክልሎች እንዲሁም አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ ፌዴሬሽኑ ብስራት የሚል ስያሜ በመስጠት ያቋቋማቸው የታዳጊ ወጣቶች ልማት ፕሮግራሞች የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር የፈቃድ አሰጣጥ ደንብ የሚጠይቀውን ዝርዝር መስፈርት ሳያሟሉ የተቋቋሙ መሆናቸውን፣ በ2006 ዓ.ም የአሰልጣኝ ክፍያና ኳሶችን ከመስጠት ባለፈ ምንም አይነት ክትትል ያልተደረገላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም የአለም አቀፉ እግር ኳስ ማህበር (FIFA) በየዓመቱ 250,000 ዶላር ለታዳጊዎች ልማት (Youth Development) ብቻ የሚልክ ቢሆንም ለታዳጊዎች ልማት ለመዋሉ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃው አልቀረበም፡፡ በተጨማሪም በናሙና ከታዩ ፕሮጀክቶች ለመረዳት እንደተቻለው ድጋፍ በጠየቁ ጊዜም ቢሆን አግኝተው እንደማያውቁ ገልጸዋል፡፡

53. ስለሁኔታው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠይቀው በ2005 ዓ.ም የተደረገው የመስክ ምልከታን መሰረት ያደረገ የሁለት ቀን የውይይት መድረክ ማዘጋጀቱን፣ ለሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የፕሮጀክት ስልጠና ምዘናና ግምገማ ውጤታቸውን ፌዴሬሽኑ አጠናቅሮ ለፌደራል ስፖርት ኮሚሽን የላከ መሆኑንና ኮሚሽኑም ለየክልሉ መላኩን፣ ካፍ በታዳጊ ፕሮጀክቶች ዙሪያ የሚሰጠው ፈቃድ አለመኖሩን በተላከላቸው

ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የተጠየቁት ፕሮጀክቶች ሲቋቋሙ የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች አሟልተው በፌዴሬሽኑ ለምን ፈቃድ እንዳልተሰጣቸው ስለሆነ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

54. ይሁን እንጂ የአፍሪካ የእግር ኳስ ማህበር የፈቃድ አሰጣጥ ደንብ አንቀጽ 8/1 ላይ የታዳጊ ፕሮጀክቶች ሲቋቋሙ ማሟላት ያለባቸውን ነገሮች ያስቀመጠ በመሆኑ ፣ እንዲሁም በየክልሉ የሚገኙ የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶች የመስክ ክትትልና ግምገማ በማድረግ ግብረ-መልስ መላክን በተመለከተ በ2006 ዓ.ም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በሀረሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስትና በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመስክ ክትትል ቢደረግም የግብረ-መልስ የተላከ ስለመሆኑ እና ከ2005 - 2007 ዓ.ም ድረስ በሌሎች ክልሎች የመስክ ክትትል በማድረግ የግብረ-መልስ ስለመላኩ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

55. ፌዴሬሽኑ የታዳጊ ወጣቶች ልማት ፕሮግራም ለማቋቋም ፍቃድ ለሚጠይቁ አካላት አገሪቱ አባል የሆነችበትን የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር የፈቃድ አሰጣጥ ደንብ የሚጠይቀውን ዝርዝር መስፈርት ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ፈቃድ የማይሰጥ ከሆነ በታችኛው ዕድሜ ክልል ያሉ ሰልጣኞች በዕድሜ ደረጃቸው ማግኘት ያለባቸውን ደረጃውን የጠበቀ ሥልጠና እንዳያገኙ የሚያደርጋቸው በመሆኑ ለእግር ኳስ ስፖርቱ እድገት ወሳኝ የሆኑ የወደፊት ተተኪዎችን እንዳይኖሩ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም በየክልሉ የሚካሄዱ የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶችን በየዓመቱ ክትትልና ግምገማ በማድረግ ፕሮጀክቶች በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ በግብረ መልስ ሪፖርት የማያሳውቃቸው ከሆነ ድክመታቸውን በወቅቱ እንዳያርሙ፣ ለሚያጋጥሙአቸው ችግሮች በወቅቱ መፍትሄ እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡

## ክለቦች በአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር እና በአለም አቀፍ እግር ኳስ ማህበር የሚጠይቋቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላታቸውን እና ሂሳባቸውን ማስመርመራቸውን በተመለከተ፣

56. ፌዴሬሽኑ ማንኛውም ክለብ ሲቋቋም የአፍሪካ እግር ኳስ ማኀበር (CAF) እና የዓለም አቀፍ እግር ኳስ ማኀበር (FIFA) ደረጃ እና የፈቃድ አሰጣጥ የሚጠይቀውን ቅድመ

ሁኔታ ማሟላቱን እና በየዓመቱ የገቢና ወጪ ሂሳቡን በውጭ ኦዲተር ማስመርመሩን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

57. በኦዲት ወቅት በናሙና የታዩ ክለቦች (ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ቡና፣ ቡራዩ፣ ሰበታ፣ ወልዋሎ እና መቀሌ) የአፍሪካ እግር ኳስ ማኅበር (CAF) እና የዓለም አቀፍ እግር ኳስ ማኅበር (FIFA) ደረጃ የሚጠይቀውን ቅድመ ሁኔታዎች (የተሟላ ጽ/ቤትና በሙያው የሰለጠነ ባለሙያ፣ በቂ በጀት፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታ፣ የባንክ አካውንት ወዘተ) በማሟላት ያልተቋቋሙ መሆናቸው ታውቋል፡፡ ከነዚህ ክለቦች ውስጥ ከቅዱስ ጊዮርጊስና ከኢትጵያ ቡና እግር ኳስ ክለቦች በስተቀር ሌሎቹ ክለቦች በተለያዩ የመንግሰት ድርጅቶች እና የከተማ መስተዳድሮች ያቋቋማቸው በመሆናቸው ከእነርሱ ከሚመደብላቸው በጀት በስተቀር የሚያስተዳድሩት በጀት የሌላቸው በመሆኑ በውጭ ኦዲተር ሂሳባቸውን የማያስመረምሩ መሆኑ ታውቋል፡፡

58. ስለሁኔታው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠይቆ በሀገሪቱ የሚገኙ ክለቦች የአፍሪካ እግር ኳስ ማኅበር (CAF) የፈቃድ አሰጣጥ ደንብ እና የዓለም አቀፍ እግር ኳስ ማኅበር (FIFA) ደረጃ ቅድመ ሁኔታዎች የማያሟሉ መሆናቸውን እንደሚያምኑ ነገር ግን ሁሉም ክለቦች በላይሰንሱ ላይ የተቀመጡትን ለማሟላት አቅሙ የሌላቸው መሆኑና ቅድመ ሁኔታዎችን እንዲያሟሉ ቢገደዱ ሊፈርሱ እንደሚችሉ ፌዴሬሽኑ ስለሚያምን ቅድመ ሁኔታዎችን እንዲያሟሉ የማያስገድድ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የክለቦች ሂሳብ በውጭ ኦዲተር ማስመርመርን በተመለከተ የቁጥጥር ስርዓት ተግባራዊ ባለመሆኑ ክለቦች ሂሳባቸውን ማስመርመራቸውን ፌዴሬሽኑ ክትትል ሊያደርግ አለመቻሉን በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

59. ፌዴሬሽኑ ከላይ የተገለጸውን መልስ ቢሰጥም አገሪቱ የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር አባል እንደመሆኗ መጠን መሰራት ያለባቸውን ሁሉ እንደ አባል በማከናወን ክለቦችም ይህንን አቅም እንዲያገኙ የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ በመቅሰም ላይሰንሱ የሚጠይቃቸውን ቅድመ ሁኔታዎች እንዲያሟሉ ጥረት ማድረግ ስለሚኖርባቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

60. አብዛኞቹ ክለቦች በፈቃድ አሰጣጥ ደንቡ መሰረት ማሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች አለማሟላታቸው በአህጉር አቀፍም ሆነ አለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ውጤታማ በመሆን አገርን ለማስጠራት በሚኖረው ሂደት ላይ የራሱን የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

**በእግር ኳስ ስፖርቱ በሁሉም እድሜ ክልል ያሉ ሴቶች ተሳትፎን በተመለከተ፣**

61. ፌዴሬሽኑ በእግር ኳስ ስፖርት በሁሉም የእድሜ ክልል የሚገኙ የሴቶች ተሳትፎ (በውድድር፣ በስልጠና ወዘተ) የሚጠናከርበትን እና የሚያድግበትን ስርዓት በመዘርጋት ድጋፍና ክትትል ማድረግ አለበት፡፡

62. ይሁን እንጂ ፌዴሬሽኑ በሁሉም የእድሜ ክልል የሚገኙ ሴቶች ተሳትፎ የሚጠናከርበትን ስርዓት ያልዘረጋ እና በሁሉም እድሜ ክልል ያሉ የሴቶችን ተሳትፎ ለማጠናከር (በውድድር፣ በስልጠና… ወዘተ) በአመታዊ እቅድ በመያዝ እንዲከናወን ያላደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

63. ስለሁኔታው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ ከመንግስት ጋር በሁሉም የስፖርት አይነቶች ፕሮጀክት ውስጥ ሴቶች ተጠቃሚ መሆናቸውንና በሉሲ ማቀጣጠያ ፕሮግራም ላይ የሴቶችን ተሳትፎ እንደሚያሳድጉ በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

64. የፌደሬሽኑ የበላይ ኃላፊዎች ከላይ የተጠቀሰውን መልስ ቢሰጡም ፕሮግራሙ በየዓመቱ እየተከናወነ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ ሲሆን መንግስት ባዘጋጃቸው ፕሮጀክቶች ሴቶች ተጠቃሚ እንደሆኑ ከመግለፅ ባለፈ በራሱ ጥረት በሴቶች ዙሪያ በየዓመቱ ስላከናወናቸው ተግባራት እና ታዳጊዎች ከፕሮጀክት ጀምሮ በየደረጃ ውድድር እየተዘጋጀላቸው ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

65. ፌዴሬሽኑ ከተሰጡት ኃላፊነቶች ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ ማጠናከር አንዱ ተግባር እንደመሆኑ በዚህ ዙሪያ ራሱ ማከናወን ያለበትን ተግባራት አለማከናወኑ ሀገራችን በሴቶች ተሳትፎ ልታገኝ የምትችለውን እውቅና እንዳታገኝ ያደርጋታል፡፡

**በህፃናት እግር ኳስ ልማት ዙሪያ የተዘጋጀው ሰነድ ፌዴሬሽኑና በባለድርሻ አካላት ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

66. ፌዴሬሽኑ በህፃናት እግር ኳስ ልማት ዙሪያ ከጋራ ትብብር ኮሚቴው (ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከፌደራል

ስፖርት ኮሚሽን) ጋር በጋራ ለመስራት በተፈራረሙት ሰነድ መሰረት እቅድ በማቀድ ተግባራዊ እንዲሆን በጋራ ሊንቀሳቀሱ ይገባል፡፡

67. በኦዲቱ ወቅት ፌዴሬሽኑ ከአራቱ ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት (ፌደራል ስፖርት ኮሚሽን፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር እና ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር) በህፃናት እግር ኳስ ልማት ዙሪያ በጋራ ለመስራት የሚያስችል ሰነድ በ2006 ዓ.ም የተዘጋጀ ቢሆንም እስካሁን ተፈርሞ ወደ ተግባር ያልተገባ መሆኑ ታውቋል፡፡

68. ስለሁኔታው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠይቆ ሰነዱን ለመፈራረም እንዲቻል ከላይ ለተጠቀሱት ባለድርሻ አካላት በተደጋጋሚ ጥሪ አቅርበው ሊገኙ ባለመቻላቸው ሰነዱ ሊፈረም እንዳልቻለ በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ከላይ ለተጠቀሱት ባለድርሻ አካላት ተደጋጋሚ ጥሪ ስለመቅረቡ የሚገልጹ ማስረጃዎች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

69. ይህ ሰነድ በወቅቱ ተፈርሞ ተግባራዊ አለመደረጉ ለእግር ኳስ ልማት መሰረት የሆነው የህፃናት ልማት ስራ በአግባቡ እንዳይሰራ የሚያደርገው በመሆኑ ተተኪ ዜጎች ለማፍራት እንዳይቻል ያደርገዋል፡፡

### ፌዴሬሽኑ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣

70. ፌዴሬሽኑ በራሱ ገቢ ለማስተዳደር የሚያግዘውን የገቢ ማሰባሰቢያ ስልት ነድፎ ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡

71. ይሁን እንጂ ፌዴሬሽኑ በ2007 ዓ.ም. ዘመናዊ የማርኬቲንግ ሰርዓትን በመዘርጋት ፌዴሬሽኑ በአመት ውስጥ 138 ሚሊየን ብር ለማግኘት እንዲሁም ከ2006-11 ድረስ ባለው ስትራቴጂክ እቅዱ ውስጥ ከመንግስት 160 ሚሊየን ለማግኘት በእቅድ መያዙ ታውቋል፡፡ነገር ግን በ2007 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ከስፖንሰርሺፕ፣ ከቲኬት ሽያጭ ፣ ከማስታወቂያ፣ ከስታዲየም ዙሪያ ኪራይ ከመሳሰሉት ብር 49 ሚሊየን ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 18 ሚሊየን አምስት መቶ ሰማንያ ሰባት ሺ (38%) እንደተገኘ የተገለፀ ሲሆን የገቢ እቅዱ ከ138 ሚሊየን ወደ 49 ሚሊየን ዝቅ ብሎ

ስለመከለሱ ማስረጃው በኦዲቱ ወቅት አልቀረበም፡፡ በተጨማሪም ከመንግስት የሚጠየቀው ገንዘብ ለምን አላማ እንደሚውል ማስረጃው አልቀረበም፡፡

72. ስለሁኔታው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ የገቢ ማሰባሰቢያ ስራዎችን እየሰሩ መሆናቸውን ነገር ግን ያላቸው የፋይናንስ አቅም አነስተኛ በመሆኑ ከመንግስት ድጎማ በአጭር ጊዜ መላቀቅ የማይችሉ በመሆኑ በስትራቴጂክ እቅዱ ላይ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን እንዲሰጠው ለመጠየቅ በእቅድ መያዙን በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

73. የፌዴሬሽኑ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ይህን ይበል እንጂ በፌዴሬሽኑ የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ፌደሬሽኑ የተለያዩ የገቢ ማሳባሰቢያ ስልቶችን በመንደፍ ቀስ በቀስ ከመንግስት ድጎማ መላቀቅ እንዳለበት የተቀመጠ መሆኑ እና ፌዴሬሽኑ ካስቆጠረው ዕድሜ አንጻር እንዲሁም በእንቅስቃሴው ውስጥ የመንግስት ጣልቃ ገብነት መኖር የለበትም ከሚለው አቋሙ ጋር የተቃረነ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አንቀበለውም፡፡

74. ፌደሬሽኑ የራሱን የሆነ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞችን በመንደፍ እራሱን የሚችልበትን ሁኔታዎች ላይ በስፋት አለመስራቱ ከመንግስት ድጎማ እንዳይወጣ፣ ስፖርቱም ህዝባዊ መሰረት እንዳይኖረውና በፊፋ ደረጃ የተቀመጠውን ከመንግስት ገለልተኛ ስለመሆን የሚደነግገውን መርህ እንዲጥስ ያደርገዋል፡፡

## ፌዴሬሽኑ የሚያሰራቸውን የግንባታ ስራዎች በተመለከተ፣

75. ፌዴሬሽኑ ለሚያሰራቸው ማንኛውም የግንባታ ፕሮጀክቶች ግልጽነት ባለው መልኩ ተወዳዳሪዎችን በማወዳደር የስራ ተቋራጮችን በፌዴሬሽኑ የጨረታ ሕግ መሰረት ሊመርጥ ይገባል፡፡

76. ፌዴሬሽኑ ለሚያሰራው ማንኛውም የግንባታ ፕሮጀክቶች በፌዴሬሽኑ የጨረታ ሕግ መሰረት መፈፀም ያለበት ቢሆንም ሲ.ኤም.ሲ አካባቢ የሚገኘው የአፍርካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን ለምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ አገሮች የእግር ኳስ የአካዳሚ ህንፃ ፕሮጀክት ግቢ አጥር ለማስገንባት የተላከውን 250,000 የአሜሪካን ዶላር ያለጨረታ ለአንድ ድርጅት የተሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

77. ስለሁኔታው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫው ላይ በሰጠው ምላሽ ይህ ጉዳይ ቀድሞ በነበሩ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተፈፀመ በመሆኑ በዚህ ዙሪያ በቂ መረጃ እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የተጠየቀው የተቋሙን

አሰራር እንጂ የግለሰቦች አመለካካት ባለመሆኑ እና የተወሰኑት መረጃዎች በፌዴሬሽኑ ይኖራሉ ተብሎ ስለሚታመን የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

78. ፌዴሬሽኑ ያሰራውን የእግር ኳስ የአካዳሚ ህንፃ ፕሮጀክት ግቢ አጥር ግንባታ ፕሮጀክት ያለ ምንም ውድድር እና በቂ ምክንያት ለአንድ ድርጅት መስጠቱ በግልጽነት የፌዴሬሽኑን ሀብት ማስተዳደርን ጥያቄ ውስጥ ከማስገባቱም በላይ ለብልሹ አሰራሮች የተጋለጠ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

## 2.2 በሀገሪቱ የእግር ኳስ ስፖርትን ለመምራትና ለማስተዳደር ቀልጣፋና ውጤታማ የሥልጠናና የውድድር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መሆኑን ማጣራት፣

### በፌዴሬሽኑ የሚሰጡ ስልጠናዎች የክልሎችንና የክለቦችን የስልጠና ፍላጎት ያገናዘበ ስለመሆኑ፣

79. ፌዴሬሽኑ የአሰልጣኝነትና የዳኝነት ስልጠና ለመስጠት መርሐ-ግብር ከማውጣቱ በፊት የክልሎችና የክለቦችን የስልጠና ፍላጎት (የስልጠናው ይዘት፣ የሚወስደው የጊዜ መጠን፣ የትምህርት ዝግጅት ወዘተ) የደሰሳ ጥናት በማካሄድ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

80. በኦዲቱ ወቅት በ2006 ዓ.ም ፌዴሬሽኑ ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች (ቤንሻንጉል፣ የኢትዮጵያ ሶማሌ፣ አፋርና ጋምቤላ) ብቻ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ማከናወኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በናሙና ከታዩ የክልል የእግር ኳስ ክለቦች እንደገለጹት ፌዴሬሽኑ የአሰልጣኝነትና የዳኝነት ስልጠና ለመስጠት መርሐ-ግብር ከማውጣቱ በፊት የእነርሱን የስልጠና ፍላጎት ግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

81. የስልጠና ፍላጎት ለየክልሎች የማይላክ በመሆኑ (የስልጠናው ዓይነት፣ መሳተፍ ያለበት የሰው ብዛት እና የመሳሰሉትን) ክልሎች ሊያውቁ ባለመቻላቸው በተደጋጋሚ አንድን ስልጠና ለአንድ ሰው የመስጠትና የመሳሳሉት ችግሮች እንዳሉ ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

82. የፌዴሬሽኑ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተጠይቆ ክልሎች ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ በመሆኑ የስልጠና ፍላጎታቸውን የመጠየቅ ግዴታ እንደሌለባቸው በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን

ይበሉ እንጂ ከፌዴሬሽኑ ሥልጣንና ተግባር መካከል አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልልም ሆነ በፌዴራል ስፖርቱ እንዲስፋፋና እንዲያድግ ድጋፍ ማድረግ በመሆኑ ተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

83. ፌደሬሽኑ በፌዴራል ደረጃም ሆነ የሁሉንም ክልሎች የስልጠና ፍላጎት (need assessement) ባለመጠየቁ ሰልጣኞች ስልጠናውን በተደጋጋሚ በመውሰድ የመሰላቸትና ለስራቸው አዳዲስ ስልጠናዎችን እንዳያገኙ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ለአሰልጣኞችና ለዳኞች መስፈርት ተዘጋጅቶ ደረጃ መሰጠቱን በተመለከተ፣

84. ፌዴሬሽኑ የአሠልጣኞችና የዳኞችን ደረጃ የሚያረጋግጥ መስፈርት ሊያዘጋጅ፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የሚዘጋጀውም መስፈርት አገሪቱ አባል የሆነችበትን የአለም አቀፉን የእግር ኳስ ማህበር(FIFA) እና የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር (CAF) ጋር የተጣጣመ ሊሆን ይገባል፡፡

85. ይሁን እንጂ ፌዴሬሽኑ ለእግር ኳስ ዳኞች ደረጃ የሚሰጥበት መስፈርት ቢኖረውም ለአሰልጣኞች የሚሰጠው ደረጃ ከአለም አቀፍ የደረጃ አሰጣጥ ጋር የማይጣጣም እና መስፈርቱን የማያሟላ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

86. ስለጉዳዩ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጠው ምላሽ በአገር አቀፍ ደረጃ 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ አሰልጣኝነት ስልጠና ምዘና በማከናወን ሰርተፍኬት በመስጠት ማረጋገጫ እየተሰጠ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በተሰጠው ምላሽ ደግሞ የአሰልጣኞች ደረጃ በአምስት የተለዩ መሆናቸውን የገለጹና ማስረጃ የተያያዘ ቢሆንም የሚሰጠው ደረጃ ከአለም አቀፉ የደረጃ አሰጣጥ ጋር ለምን እንዳልተጣጣመ ምላሽ አልሰጡም፡፡

87. የአለም አቀፉን የእግር ኳስ ማህበር መመዘኛ መስፈርት በመጠቀም ለአሰልጣኞቹ ደረጃ እንዲሰጥ አለማድረጉ እና የአሰልጣኞችን የሙያ ብቃት አለማረጋገጡ ስፖርቱ ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች እንዳይመራ የሚያደርግ እና የእግር ኳስ ስፖርቱንና ክለቦችን ለማሳደግ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡

### የብሔራዊ ቡድን አሰልጣኞች መመልመያ መስፈርትን በተመለከተ፣

88. ፌዴሬሽኑ የአገሪቱን ብሔራዊ ቡድኖችን የሚያሰለጥኑ አሠልጣኞችን ለመምረጥ የሚያስችል ግልፅ የሆነ የመመልመያ መስፈርት/መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ የሚያወጣውም መስፈርት ቢያንስ የአለምአቀፉን የእግር ኳስ ማህበር የአሰልጣኝነት መስፈርት የሚያሟሉ ሊሆኑ ይገባል፡፡

89. ይሁን እንጂ በፌዴሬሽኑ በሁሉም ጾታ የብሔራዊ ቡድኖችን (የአዋቂ፣ ከ 23 አመት በታች፣ ከ21 አመት በታች፣ ከ17 ዓመት በታች፣ የታዳጊ፣ ወዘተ...) የሚያሰለጥኑ አሠልጣኞችን ለመምረጥ የሚያስችል ግልፅ የሆነ የመመልመያ መስፈርት/መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም ፌዴሬሽኑ ለሁሉም ብሔራዊ ቡድኖች የአሰልጣኞች ቅጥር መፈጸም በሚፈለግበት ጊዜ የቴክኒክ ኮሚቴው እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው በሚያወጣቸው መመዘኛዎች መሰረት የቅጥር ማስታወቂያ በማውጣት የሚመረጥ መሆኑ ታውቋል፡፡

90. ስለሁኔታው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጠው ምላሽ አሰልጣኞችን ወቅታዊ በሆኑ ተለዋዋጭ መስፈርቶች መምረጡ አስፈላጊ በመሆኑ ቋሚ የሆነ መመሪያ ማዘጋጀቱ አስፈላጊ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ የፌዴሬሽኑ የአስልጣኞች የመመልመያ መስፈርት አዘጋጅተናል በማለት አያይዘው የቀረቡት ማስረጃ በቀድሞው በስፖርት ኮሚሽን ለሁሉም ፌዴሬሽኖች በ2006 ዓ.ም የተዘጋጀ ረቂቅ ሰነድ እንጂ በየደረጃው ላሉ ለሁለቱም ጾታዎች የእግር ኳስ ብሔራዊ ቡድኖች የሚቀጠሩ አሰልጣኞች መምረጫ መስፈርት ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

91. የብሔራዊ ቡድኖች አሰልጣኝ የመምረጫ መስፈርት እንደ የደረጃቸው አለመዘጋጀቱና በየጊዜው በቴክኒክ ኮሚቴው መመረጡ ፌዴሬሽኑ የሚያከናውነው ምርጫ ሁሉም በግልጽ ሊረዳው በሚችል መልኩ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ ምርጫው አድሎአዊ ለሆኑ አሰራሮች እንዲጋለጥ ሊያደርገው ይችላል፡፡

## በፕሮጀክቶች የታቀፉ ታዳጊ ሰልጣኞች በሥልጠና ወቅት ለሚያጋጥማቸው ጉዳት  የህክምና አገልግሎት ስለመሰጠቱ፣

92. በፕሮጀክቶች የታቀፉ ታዳጊ ሰልጣኞች ከሥልጠናው ጋር በተያያዘ ለሚያጋጥማቸው ጉዳት የህክምና አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

93. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ካየናቸው በኦሮሚያ፣ በትግራይ ክልልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር ስር ከሚገኙ  በታዳጊ ፕሮጀክቶች የታቀፉ ታዳጊ ሰልጣኞች ከሥልጠናው ጋር በተያያዘ ለሚያጋጥማቸው ጉዳት የህክምና አገልግሎት ያልተዘጋጀ መሆኑ በመስክ ጉብኝት ወቅት ታውቋል፡፡

94. ስለሁኔታው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ  ከስፖርት ኮሚሽን፣ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በጋራ የተዘጋጀውን ሰነድ ተፈርሞ ስራ ላይ ባለመዋሉ ምክንያት የህክምና አገልግሎት ሊዘጋጅ አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

95. በፕሮጀክቶች የታቀፉ ታዳጊ ወጣቶች በልምምድ ወቅት ለሚያጋጥማቸው ጉዳት የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ አለመደረጉ ሠልጣኞች ከጉዳታቸው አገግመው ወደ ስልጠናው በመመለስ ወደ ተሻለ ስራ እንዳይገቡ ያደርጋቸዋል፡፡

## ፌዴሬሽኑ የሚያዘጋጃቸው የአገር አቀፍ ውድድሮች የአለም አቀፉን የእግር ኳስ ማህበር የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ፣

96. ፌዴሬሽኑ የሚያዘጋጃቸው በሁሉም ሊጎች የአገር አቀፍ ውድድሮች የአለም አቀፉን የእግር ኳስ ማህበር የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በማድረግ ሊያዘጋጅ እና መርሐ ግብሮቹም የክለቦችን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ሊሆን ይገባል፡፡

97. ይሁን እንጂ ፌዴሬሽኑ በሁለቱም ጾታዎች የሚያዘጋጃቸው የሁሉም ሊጎች የአገር አቀፍ ውድድሮች የአለም አቀፉን የእግር ኳስ ማህበር የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የማያደርግ መሆኑ፣ በየውድድር ዓመቱ የሚያወጣቸው የሊጎች የውድድር መርሐ-ግብር የሁሉንም ክለቦች ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ በመሆኑ ለምሳሌ ከሞላ ጎደል ሁሉም ክለቦች በጀታቸው የተመሰረተው ከመንግስት በመሆኑ የበጀት ዓመቱም የሚያልቀው በሰኔ ወር መጨረሻ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የፌዴሬሽኑ የውድድር ፕሮግራም ግን ሐምሌና ነሐሴ ድረስ የሚሄድ በመሆኑ ክለቦች ከተጫዋቾች ጋር ከሚዋዋሉት የኮንትራት ጊዜና

የዝውውር መብት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳደረ ከመሆኑም በላይ ለተጨማሪ የተጫዋቾች ክፍያ ወጪ እየተዳረጉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ያየናቸው ክለቦች ገልፀዋል፡፡

98. ስለሁኔታው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ የፊፋንና የካፍን ካላንደር (የጊዜ ሰሌዳ) መሰረት እያደረገ የውድድር ፕሮግራም በማዘጋጀት እንደሚያወዳድር ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ ከሰጡት ምላሽ ጋር የውድድር ፕሮግራሞችን አያይዘው ያቀረቡ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ያነጋገርናቸው ክለቦች፣ አሰልጣኞች እና ተጫዋቾች በሰሌዳው መሰረት እንደማይካሄድ የገለፁ ሲሆን በወጣው ፕሮግራም መሰረት ውድድሮቹ ተካሂደው በተባለላቸው ጊዜ ስለመጠናቀቃቸው ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

99. ፌደሬሽኑ የሚያወጣቸው የሊግ ውድድሮች የፊፋን ካላንደር/የጊዜ ሰሌዳ/ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ጨዋታዎች ሊቆራረጡና ክለቦችን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግና ውድድሩም ወደ ክረምት ወቅት በመግፋቱ ከመጫወቻ ሜዳ ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ችግር ይፈጥራል፡፡

## የፌዴሬሽኑ የተለያዩ ግንባታዎች አፈፃፀምን በተመለከተ ፤

100. ፌዴሬሽኑ የስታዲየም፣ የማሰልጠኛ ማዕከላትና የቢሮ የግንባታ በእቅድ ይዞ ሊያከናውን ይገባል፡፡

101. ይሁን እንጂ ፌዴሬሽኑ የራሱ የሆነ ስታዲየም በእቅድ ይዞ ያልገነባ፣ የማሰልጠኛ ማዕከላት ስለመገንባታቸው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ እና ከአለም አቀፍ እግር ኳስ ማህበሩ በተመደበው በጀት የቢሮ የግንባታ አለመጀመሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

102. ስለሁኔታው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጠው ምላሽ የአለም አቀፍ እግር ኳስ ማህበሩ በ2015/2007 ለቢሮ ግንባታ የመደበው 500,000 USD ፌዴሬሽኑ ለግንባታው በቂ ሆኖ ስላላገኘው ወደ አፈፃፀም አለመግባቱን የስታዲየም የማሰልጠኛ ማዕከላት ግንባታን በተመለከተ የክለቦችና የመንግስት ኃላፊነት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ለቢሮ ግንባታው በእርዳታ በተገኘው ገንዘብ ስራውን በመጀመር ተጨማሪ ገቢ ለማፈላለግ ጥረት ማድረግ ይቻል ስለነበረ እና ፌዴሬሽኑ መስከረም 2006 አሻሽሎ ባወጣው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 33 ቁጥር 3 ላይ ‹ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን የማቋቋምና

የማሰፋፋት፣ የፌዴሬሽኑ ስልጣንና ተግባር መሆኑ የተገለጸ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

103. ፌዴሬሽኑ ካስቀጠረው እድሜ አንፃር የስታዲየምና ማሰልጠኛ ማዕከላት ግንባታ ለማድረግ እንቅስቃሴ አለመጀመሩ፣ የተገኙ እርዳታዎችን በመጠቀም የቢሮ ግባታዎችን አለመፈፀሙ አገሪቱ ያለባትን የስታዲየምና የማስልጠኛ ማዕከላት እጥረት ችግር እንዳይቃለል፣ የቢሮው ግንባታ በማጠናቀቅ የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

## የፀረ-ዶፒንግ /አበረታች መድሐኒቶች/ኮንቬንሽን ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣

104. ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው የአገር ውስጥ ውድድሮች እንዲሁም በሁሉም ክልሎች እና የከተማ መስተዳድሮች ላይ የፀረ-ዶፒንግ /አበረታች መድሐኒቶች /ኮንቬንሽን ተግባራዊ የሚደረግበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊነቱን መከታተል አለበት፡፡

105. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ፌዴሬሽኑ የፀረ-ዶፒንግ /አበረታች መድሐኒቶች/ኮንቬንሽንን ተግባራዊ የሚያደርግበት ሥርዓት በሚያዘጋጃቸው የአገር ውስጥ ውድድሮች እንዲሁም በሁሉም ክልሎች እና የከተማ መስተዳድሮች ተግባራዊ እንዲሆን ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

106. ስለሁኔታው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጠው ምላሽ የፀረ-ዶፒንግ ተግባርን የሚያከናውን ራሱን የቻለ ኮሚቴ ተቋቁሞ እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የኮሚቴው መቋቋሚያ ሰነድ፣ የኮሚቴውን ተጠሪነት፣ ስልጣንና ተግባር፣ እንዲሁም የኮሚቴው የስብሰባ ቃለ-ጉባኤ እና ያቀረባቸው ሪፖርቶች፣ ሥራውን የሚሰራበት የተሚላ ላብራቶሪ (ከሌላ ተቋም ጋር የገባው ውል) ስለመኖሩ፣ ወዘተ እንዲቀርቡ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

107. ፌደሬሽኑ የፀረ-ዶፒንግ /አበረታች መድሐኒቶች/ ኮንቬንሽንን ተግባራዊነት ካላደረገ በውድድሮች ላይ ተጨዋቾች በአበረታች መድሐኒቶች እንዳይጠቀሙ መከላከልን እና ጤናማ ዜጋ ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

**የሽልማት አሰጣጥ መመሪያን በተመለከተ፣**

108. ፌዴሬሽኑ የእግር ኳስ ክለቦችን፣ ባለሙያዎችን እና ተጨዋቾችን ለማበረታታትና እውቅና ለመስጠት የሚያስችል ግልፅና ወጥ የሆነ የሽልማት አሰጣጥ መመሪያ ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ መመሪያውም ለየትኛው ስራ ምን አይነት ሽልማት የሚለውን በግልጽ ሊያስቀምጥ እና በየአመቱ ዕቅድ ውስጥ ሊካተት ይገባል፡፡

109. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ፌዴሬሽኑ የእግር ኳስ ክለቦችን እና ተጨዋቾችን እና ሌሎች ባለሙያዎችን ለማበረታታትና እውቅና ለመስጠት የሚያስችል ግልፅና ወጥ የሆነ የሽልማት አሰጣጥ መመሪያ የሌለውና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በየጊዜው ስብሰባ በማድረግ በሚሰጠው ውሳኔ ብቻ የሚሸልም መሆኑ ታውቋል፡፡

110. ስለሁኔታው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጠው ምላሽ ብሔራዊ የቴክኒክ ኮሚቴ የኮከብ ተጫዋቾች መምረጫ መስፈርት አውጥቶ በስራ ላይ እንዳዋለ ገልጸው የኮከብ ተጫዋቾችን ለመምረጥ የሚያስችል ማስረጃ አያይዘው ልከዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የኮከብ ተጫዋቾችን ለመምረጥ የሚያስችል መምረጫ መስፈርት የተዘጋጀ መሆኑን ያረጋገጥን ቢሆንም የእግር ኳስ ክለቦችን፣ ባለሙያዎች እና ተጨዋቾችን ለማበረታታትና እውቅና ለመስጠት የሚያስችል የሽልማት አሰጣጥ መመሪያ ለኦዲቱ ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

111. ፌዴሬሽኑ በየጊዜው የሚሰጣቸው ሽልማቶች መመሪያዎችን መሰረት ባለማድረጋቸው ለሽልማት የሚወጡ ገንዘቦችን በዕቅድ እንዳይመራ ከማድረጉም በላይ ግልጽነት የሌለው አሰራር በማስፋፋት አለአግባብ የሆነ የሀብት ብክነት እንዲከሰት በር ይከፍታል፡፡

**ብሔራዊ ቡድኑ የሚኖረውን የአቋም መለኪያ በተመለከተ፣**

112. ፌዴሬሽኑ ብሔራዊ ቡድኑ ለሚኖረው የነጥብ ጨዋታ የወዳጅነት (የአቋም መለኪያ) ጨዋታዎችን የሚያከናውንበትን ሁኔታዎች ሊያመቻች ይገባል፡፡

113. ፌዴሬሽኑ ከ2006-11 ባለው ስትራቴጂክ እቅዱ ላይ ብሔራዊ ቡድኑ ለሚኖረው የነጥብ ጨዋታ የወዳጅነት (የአቋም መለኪያ) ጨዋታዎችን ለማድረግ ቢያቅድም አለማከናወኑ ታውቋል፡፡

114. የፌዴሬሽኑ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሰጠው ምላሽ የወዳጅነት (የአቋም መለኪያ) ጨዋታዎችን አቅሙ በፈቀደ መጠን እንደሚያመቻች ቢገልፅም በስትራቴጂክ እቅዱ መሰረት በየዓመቱ ከፋፍሎ በማቀድ ያላከናወነው በመሆኑ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

115. ብሔራዊ ቡዱኑ የወዳጅነት ጨዋታዎችን አለማድረጉ አቋሙን በመለካት ያሉበትን ክፍተቶች ለይቶ በማወቅና በማሻሻል ለውጤት በሚኖሩት ጨዋታዎች ላይ ውጤታማ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ ስትራቴጂክ ዕቅዱን ሲያቅድ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ አስገብቶ ማቀዱን አጠያያቂ ያደርጉታል፡፡

## 2.3 በፌዴሬሽኑ የእግር ኳስ ስፖርትን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ አጠባበቅ፣ አጠቃቀምና ልውውጥ አጥጋቢ እና አስተማማኝ መሆኑን መገምገም፣

### በፌዴሬሽኑ መረጃዎች ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የሚሆንበት ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፣

116. የፌዴሬሽኑ እንቅስቃሴ የሚመለከቱ መረጃዎች በሙሉ ተጠናቅረው ሊያዙ ይገባል፡፡ የተጠናቀሩትም መረጃዎች የተለያዩ ተጠቃሚ ወገኖች የሚያገኙበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የመረጃ አያያዙም በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ ሊታገዝ ይገባል፡፡

117. ይሁን እንጂ ፌዴሬሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎች እና እግር ኳስ ስፖርትን የሚመለከቱ መረጃዎች ተሰብስበውና ተደራጅተው አለመያዛቸው፣ ያሉትን መረጃዎች በዘመናዊ መልክ ለማደራጀት መረጃ ቋት (data base) አዘጋጅቶ አለመያዙ፣ ያሉትን መረጃዎ መረጃውን ለሚፈልጉ አካላት እንዲያገኙ ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ አለመያዙን እንዲሁም የራሱን የሥራ እንቅስቃሴ እና የእግር ኳስ ስፖርትን የሚመለከት መረጃዎችን እና ዜናዎችን የሚያሰራጭበት መረጃ መረብ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

118. ስለሁኔታው የፌዴሬሽኑ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ በሰው ሃይልና ቁሳቁስ ችግር ምክንያት ፌዴሬሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ

መረጃዎችንና እግር ኳስ ስፖርቱን የሚመለከቱ ወቅታዊ መረጃዎች በመረጃ መረብ ተጠቃሚ ወገኖች እንዲገኙ በሚያስችል መልኩ አለመደረጉ ገልፀዋል፡፡

119. የአገሪቱን የእግር ኳስ እንቅስቃሴ የሚመለከቱ መረጃዎች ተሰብሰበውና ተጠናቅረው አለመያዛቸው፣ በዘርፉ ምርምር ለሚያደርጉ፣ በተለያየ ሁኔታ መረጃዎቹን የሚፈልጉ መረጃዎቹን በቀላሉ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

120. የእግር ኳስ ስፖርትን ለመምራት እና ለማስፋፋት ያለው የአሰራር ስርዓት ውጤታማና ብቃት ባለው መልኩ እየተተገበረ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- በፌዴሬሽኑ የተዘጋጀው የስትራቴጂክ እቅድ ነባራዊ ሁኔታን ከግምት ውስጥ ያላስገባ እና የተዘጋጀውንም ስትራቴጂክ ዕቅድ ወደ አመታዊ እቅድ እየመነዘረ ያልታቀደ መሆኑ፣
- የእቅድ ክንውን ሪፖርቱ ውስጥ አፈፃፀም ላይ የታዩ ክፍተቶችን እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ያላካተተ እና የየዓመት የእቅድ አፈፃፀሙን በወር፣ በየሩብ ዓመትና በአመቱ መጨረሻ የማይገመግም መሆኑ፣
- በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ፌዴሬሽኑ የሩብ አመት አፈጻጸም ሪፖርቱን ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር (ለቀድሞው ስፖርት ኮሚሽን) የማይልክ መሆኑ፣
- ፌዴሬሽኑ በ2006 ዓ.ም የውስጥ መዋቅራዊ አደረጃጀት እና የሰው ሃይል ፍላጎት ያስጠናውን ጥናት ተግባራዊ አለማድረጉ፣ በ2008 ዓ.ም በተከለሰው አደረጃጀት የውስጥ ኦዲትን ክፍል የተካተተ ቢሆንም ባጠቃላይ ጥናቱ በሚመለከተው አካል ያልፀደቀ መሆኑ፣
- የፌዴሬሽኑ አባላት (የክልል ፌዴሬሽኖች፣ ክለቦች ወዘተ) በመተዳደሪያ ደንብ ላይ የተቀመጡ የአባላት ግዴታዎችን ስለመወጣታቸው የሚከታተልበት ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣
- ፌዴሬሽኑ በእግር ኳስ ስፖርት ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎች የማያከናውን መሆኑ፣
- የታዳጊ ወጣቶች ልማት ፕሮግራሞች ሲቋቋሙ የአፍሪካ የእግር ኳስ ማህበር ያስቀመጠውን መስፈርት ማሟላታቸውን የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- ፌዴሬሽኑ ፈቃድ በሰጣቸው ፕሮጀክቶች ላይ ክትትልና ግምገማ ቢያደርግም የግብረ መልስ ሪፖርት የማይልክላቸው መሆኑ፣

- ክለቦች የአፍሪካ እግር ኳስ ማኅበር (CAF) እና የዓለም አቀፍ እግር ኳስ ማኅበር (FIFA) ደረጃ እና ፈቃድ አሰጣጥ ደንብ የሚጠይቀውን ቅድመ ሁኔታ ሳያሟሉ የተቋቋሙ መሆኑን፣ የክለቦች ሂሳብ በውጭ ኦዲተር ኦዲት የማይደረግ መሆኑ፣
- ፌዴሬሽኑ በሁሉም የእድሜ ክልል የሚገኙ ሴቶች የእግር ኳስ ተሳትፎ የሚጠናከርበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- ፌዴሬሽኑ በወጣቶች ልማት ዙሪያ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት (የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን፣ የጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ ከሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚ/ር እና ከትምህርት ሚኒስቴር) ጋራ በመሆን አብሮ ለመስራት የተዘጋጀው የመግባቢያ ሰነድ እስካሁን ያለተፈረመ እና ወደ ሥራ ያልተገባ መሆኑ፣
- ፌዴሬሽኑ ገቢውን ለማሳደግ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በስፋት ያላደረገ እና ከመንግስት ድጎማ ያልተላቀቀ መሆኑ፣
- ፌዴሬሽኑ ማሰልጠኛ ማዕከልን የአጥር ግንባታ ያለጨረታ እና ውድድር ለአንድ ድርጅት መስጠቱ፣
- ፌዴሬሽኑ ለሚሰጣቸው ስልጠናዎች የሥልጠና ፍላጎት የደሰሳ ጥናት የማያደርግ መሆኑ፣
- ፌዴሬሽኑ የሚሰጠው የአሠልጣኞች ደረጃና ሰርተፍኬት የአለም አቀፉን የእግር ኳስ ማህበር (FIFA እና የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር (CAF) መስፈርት ጋር የማይጣጣም መሆኑ፣
- ፌደሬሽኑ የብሔራዊ ቡድኖች የሚያሰለጥን አሰልጣኝ ለመምረጥ የሚያስችል ግልፅ የሆነ የመምረጫ መስፈርት ያላዘጋጀ መሆኑ፣
- በፕሮጀክቶች የታቀፉ ታዳጊ ሰልጣኞች የህክምና አገልግሎት የማያገኙ መሆኑ፣
- ፌዴሬሽኑ የሚያዘጋጃቸው ውድድሮች የአለምአቀፉን እግር ኳስ ማህበር እና የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበራት የጊዜ ሰሌዳ ጋር የማይጣጣም መሆኑ፣ ፌዴሬሽኑ የሊግ ውድድሮች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ የማይከናወን መሆኑ፣
- ፌዴሬሽኑ ባገኘው የእርዳታ ገንዘብ የቢሮ ግንባታ አለመጀመሩ እና የራሱ የሆነ የውድድር ማድረጊያ ሥፍራ የሌለው መሆኑ፣
- ፌዴሬሽኑ የፀረዶፒንግ/አበረታች መድሐኒቶች/ኮንቬንሽን ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- ፌዴሬሽኑ ክለቦችን፣ ባለሙያዎችን እና ተጨዋቾችን ለማበረታታት የሚመራበት ግልጽ የሆነ የሽልማት አሰጣጥ ስርዓት የሌለው መሆኑ፣

➢ ፌዴሬሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎች እና እግር ኳስ ስፖርትን የሚመለከቱ መረጃዎች ተሰብስበውና ተደራጅተው በዘመናዊ የመረጃ ቋት (data base) ያልተያዙ እና የመረጃ መረብ (ዌብ ሳይት) የሌለው መሆኑ፣

121. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሳቦች

122. የእግር ኳስ ስፖርትን ለመምራት እና ለማስፋፋት ብቃት ያለው ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡፡

- ፌዴሬሽኑ የስትራቴጂክ እቅዱን ሲያቅድ በዕቅድ ዘመኑ ውስጥ ሚስፈገልገውን ሀብት እና ምንጮቹን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊያቅድ ይገባል፡፡ የስትራቴጂክ ዕቅዱም በየአመቱ እየተመነዘረ ተግበራዊ እየተደረገ አፈጻጸሙም በየሩብ አመቱ በመገምገም ክፍተቶቹን በመለየትና የመፍትሔ አቅጣጫዎች በማስቀመጥ ውጤቱን በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡
- ፌዴሬሽኑ የአስጠናውን አዲስ የመዋቅራዊ አደረጃጀት እና የክለሳ ጥናት በአፋጣኝ ተግባራዊ ሊያደርገው ይገባል፡፡
- ፌዴሬሽኑ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የእግር ኳስ ፌዴሬሽኖች፣ ክለቦችና ፕሮጀክቶች የአለም አቀፉ እና የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበራት እንዲሚሉ ያስቀመጧቸውን ዝርዝር ቅድመ ሁኔታዎች አሟልተው እንዲቋቋሙና ወጥ የሆነ መዋቅራዊ አደረጃጀት እንዲኖራቸው የማያቋርጥ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡ ክለቦችም ሆኑ የክልል ፌዴሬሽኖቹ ሂሳባቸው በውጭ ኦዲተሮች እየተመረመረ ውጤቱ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሳቸው መደረጉን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ፌዴሬሽኑ ለእግር ኳስ ስፖርቱ ሊያግዙ የሚችሉ የተለያዩ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በእቅድ በመያዝ ሊያካሂድ፣ በሌሎች አካላት የሚከናወኑትንም በመከታተል መረጃውን በማጠናቀር ወደ ስራ ላይ የሚውሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡
- የታዳጊ ወጣቶች ልማት ፕሮግራሞች የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር የፈቃድ አሰጣጥ ደንብ የሚጠይቀውን ዝርዝር መስፈርት (የሰው ሃይል፣ የስልጠናና የውድድር አቅርቦት፣ የፋይናንስ ምንጭ፣ የተጫዋቾች ህክምና አቅርቦት ወዘተ እንዲሁም ከ15-21 እና ከ10-14 የእድሜ ክልል) ላይ ያሉ ወጣቶች መያዛቸውን እና ለፕሮጀክቱ ተግባራዊነት ተመራጩ አካባቢ የት መሆን እንዳለበት ፌዴሬሽኑ አረጋግጦ ፈቃድ መስጠት አለበት፡፡ እንዲሁም በየክልሉ የሚካሄዱ የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶችን በየጊዜው ክትትልና ግምገማ በማድረግ ያሉባቸውን ጠንካራና ደከማ ጎን በመለየት ጥንካሬያቸውን እንዲቀጥሉና ደካማ ጎናቸውን ደግሞ እንዲያሻሽሉ ለማድረግ የሚያስችል የግብረ መልስ ሪፖርት መላክ አለበት፡፡
- ፌደሬሽኑ በሀገሪቱ የሚገኙ ሁሉም ክለቦች በክለብ ደረጃ ለመቋቋም ፍቃድ ሲጠይቁ የአለም አቀፉ እና የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር የደረጃ እና የፈቃድ አሰጣጥ መስፈርት የሚጠይቀውን ቅድመ ሁኔታ (የገቢ ምንጭ፣ የማዘውተሪያ ስፍራ፣ የልምምድና

የውድድር ቁሳቁስ፣ የህክምና ማዕከል፣ የባንክ አካውንት ወዘተ) ማሟላታቸውን በማረጋገጥ እንዲቋቋሙ ማድረግ አለበት፡፡ ማንኛቸውም ክለቦች ሂሳባቸውን የተለየ የባንክ ሂሳብ በመክፈት ሊያንቀሳቅሱ ይገባል፡፡ ሁሉም ክለቦች እና ፌዴሬሽኖች የሚያንቀሳቅሱትንም ሂሳብ በውጭ ኦዲተር በማስመርመር ውጤቱን ለሚመለከታቸው አካላት መድረሱን ፌደሬሽኑ ሊከታተል ይገባል፡፡

- የሀገሪቱን የሴቶች የእግር ኳስ ስፖርቱ ትልቅ ደረጃ ለማድረስ እንዲቻል በሴቶች ዙሪያ የተለያዩ ፕሮግራሞች በመንደፍ ተሳትፎአቸውን ሊያሳድግ፣ ከታዳጊ ጀምሮ በየደረጃው ውድድር በማዘጋጀት ተሳትፎቸው እንዲጠናከር ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጋር በመሆን ከፍተኛ እገዛ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ፌዴሬሽኑ በህፃናት ልማት ፕሮግራም ዙሪያ ከወጣቶችና ስፖርት ሚ/ር፣ የጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ ከሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚ/ር እና ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በጋራ ለመስራት የተዘጋጀውን የመግባቢያ ሰነድ እንዲፈረም እና ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ በልማቱ ህፃናቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ አለበት፡፡
- ፌዴሬሽኑ በተደረገው የመዋቅር ጥናት መሰረት በራሱ ገቢ ለማግኘት የሚያግዘውን የገቢ ማስገኛ ዕቅዱን ከስትራቴጂክ ዕቅዱ ጋር በማጣጣም የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን እና ምንጮችን በመፈለግ ገቢውን ሊያሳድግና ከመንግስት ድጎማ ሊላቀቅ ይገባል፡፡
- ፌዴሬሽኑ በየጊዜው ለሚያደርጋቸው ማናቸውም ግንባታዎች ሆኑ ሌሎች የግዥ እና የአገልግሎት ግዥዎች በፌዴሬሽኑ የጨረታ ሕግ መሰረት ተግባራዊ በማድረግ ለምዝበራ እና ለሙስና የሚያጋልጡ አሰራሮችን ሊያስወግድ ይገባል፡፡
- ፌዴሬሽኑ የአሰልጣኝነትና የዳኝነት ስልጠና ፌዴሬሽኑ ለሚሰጣቸው ስልጠናዎች የሥልጠና ፍላጎት የደሰሳ ጥናት በማከናወን የሥልጠና ዕቅድ እና መርሐ-ግብር ሊያወጣ ይገባል፡፡
- ፌዴሬሽኑ የሚሰጠው የአሠልጣኞች ደረጃና ሰርተፍኬት የአለም አቀፉን የእግር ኳስ ማህበር እና የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር (CAF) መሰፈርትን ጋር በማጣጣም የደረጃ አሰጣጥ ሥርዓቱን ሊያስተካክል ይገባል፡፡
- ፌደሬሽኑ የብሔራዊ ቡድኖቹን አሰልጣኞች ለመምረጥ የሚያስችል ግልጽ እና ወጥ የሆነ የመምረጫ መስፈርት/መመሪያ/ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ እና መስፈርቱንም የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ እንዲያውቁት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡

- በፕሮጀክቶች ለታቀፉ ታዳጊ ሰልጣኞች ከስልጠና ጋር በተያያዘ የሚያጋጥማቸውን ጉዳት ለማከም የሚያስችል የተሟላ የህክምና አገልግሎት በየማዕከላቱ ወይንም ከአካባቢው መስተዳድሮች ጋር በመቀናጀት እርዳታ የሚያገኙበት ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ፌዴሬሽኑ የሚያዘጋጃቸው ውድድሮች የአለምአቀፉን እና የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበራት የጊዜ ሰሌዳ ጋር በማጣጣም ለሚያካሂዳቸው ውድድሮች ሁሉ የጊዜ ሰሌዳ ሊወጣ ይገባል፡፡ ውድድሮቹም በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በማከናወን ክለቦች በእቅድ ላልተያዘ ተጨማሪ ወጪ እንዳይዳረጉ፣ ከተጫዋቾች ውል እና ዝውውር ጋር በተያዙ የሚነሱ ቅሬታዎች እና አለመግባባቶች የሚወገድበትን አሰራራ በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ፌዴሬሽኑ ከአለም አቀፉ የእግር ኳስ ማህበር ባገኘው የ500,000 የአሜሪካን ዶላር የእርዳታ የቢሮ ግንባታውን ሊጀምር እና ግንባታውን ለማጠናቀቅ የሚስፈልገውን ቀሪ ገንዘብ የሚገኝበት የፋይናንስ ምንጭ በመፈላለግ ግንባታውን ሊጠናቀቅ እና አገልግሎቱን የተቀላጠፈ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪም ፌዴሬሽኑ መስከረም 2006 አሻሽሎ ባወጣው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች የሚቋቋምበት እና የሚሰፋፉበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ፌዴሬሽኑ የፀረ-ዶፒንግ /አበረታች መድሐኒቶች/ ኮንቬንሽን ተግባራዊነትን ለማጠናከር፣ ለመተግበርም ሆነ ለማስተግበር የሚያስችሉትን በፀረ-ዶፒንግ ዙሪያ ለስፖርተኞች፣ ለአሰልጣኞች ለቡድን መሪዎች ለሀኪሞች ለወጌሻዎች እና ለዳኞች ተከታታይነት ያለው ትምህርትና ስልጠና በመስጠት፣ በፀረ- ዶፒንግ የተደራጀ ወይም አገልግሎት መስጠት የሚችል ሀይል (የህክምና ኮሚቴ) በማዘጋጀት፣ በፀረ-ዶፒንግ ስፖርተኞች የሽንት/የደም ምርመራ ማድረግ እና በፀረ-ዶፒንግ ጥናትና ምርመር (ምን ያህል ስፖርተኞች ተጠቂ እንደሆኑ፣ በአበረታች መድሃኒት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ መሰጠት) የሚሉትን ተግባራት የሚከታተልና የሚያስፈፅም ራሱን የቻለ ክፍል በማቋቋም ሁሉም ክልሎች እና የከተማ አስተዳድሮች የፀረ-ዶፒንግ /አበረታች መድሐኒቶች/ ኮንቬንሽንን እንዲተገብሩ የሚደረግበትን ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ፌደሬሽኑ በሚያደርገው የማበረታቻና እውቅና መስጠት መርሀ ግብር በመተተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ግልጽ እና ወጥ የሆነ የሽልማት አሰጣጥ ስርዓት


/መመሪያ/ በማዘጋጀት በመመሪያው መሰረት በማከናወን የፋይናንስ አጠቃቀሙን በዕቅድ ሊመራ ይገባል፡፡

- ፌዴሬሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎች እና እግር ኳስ ስፖርትን የሚመለከቱ መረጃዎች ተሰብስበውና ተደራጅተው በዘመናዊ መልክ በመረጃ ቋት (data base) ሊያዙ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የመረጃ ሥርዓቱን ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድርግ ፌዴሬሽኑ የራሱን የመረጃ መረብ በመዘርጋት ተግባረዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

123. በመጨረሻም ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን፣ በኦዲት ወቅት ለታዩት፣ ለአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌደሬሽን፣ ለቅዱስ ጊዮርጊስ እና ለኢትዮጵያ ቡና እግር ኳስ ክለቦች፣ ፣በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአምቦ ጎል ፕሮጀክት፣ የሰበታ ከነማ እግር ኳስ ክለብ፣ የቡራዩ ከነማ እግር ኳስ ክለብ፣ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣ የእግር ኳስ ፌዴሬሽን፣ የዳኖችና የአሰልጣኞች ማህበር፣ የመቀሌ ከነማና የወልዋሎ እግር ኳስ ክለቦች፣ የሥራ ኃላፊዎች፣ አሰልጣኞችና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

**አባሪ 1**

## <u>የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ድርጅታዊ መዋቅር</u>



## አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች | የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች */Evaluative Criteria/* |
|---|---|
| 1. የእግር ኳስ ስፖርትን በሀገር አቀፍ ደረጃ በማስፋፋት ብቁ እና ተተኪ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ለማፍራት የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን፣ የተዘረጋውም የአሠራር ሥርዓት አጥጋቢና ውጤታማ መሆኑን ማጣራት፣ | 1.ፌዴሬሽኑ በሁሉም ክልሎች እና የከተማ መስተዳድሮች የእግር ኳስ ስፖርትን በኃላፊነት የሚያንቀሳቅሱ አካላት እንዲቋቋሙና እንዲደራጁ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2.ፌዴሬሽኑ በመተዳደሪያ ደንብ ላይ የተቀመጡ ግዴታዎች አባላቱ መወጣታቸውን የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 3.ፌዴሬሽኑ በእግር ኳስ ስፖርት ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ሊያካሂድና ሲጸድቁም ተግባራዊ ሊያደርጋቸውይገባል፡፡ |
| | 4.የታዳጊ ወጣቶች ልማት ፕሮግራም ለማቋቋም ፍቃድ የሚጠይቁ አካላት በአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር የፈቃድ አሰጣጥ ደንብ ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል፡፡ (ከ A-H የተጠቀሱትን (የሰው ሃይል፣ የስልጠናና የውድድር አቅርቦት፣ የፋይናንስ ምንጭ፣ የተጫዋቾች ህክምና አቅርቦት ወዘተ) እንዲሁም ከ15-21 እና ከ10-14 የእድሜ ክልል ላይ ያሉ ወጣቶች መያዛቸውን እና በየክልሉ ተግባራዊ ሊደረጉ ስለመቻላቸው በፌዴሬሽኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ |
| | 5.ፌዴሬሽኑ በእግር ኳስ ስፖርት በሁሉም የእድሜ ክልል የሚገኙ የሴቶች ተሳትፎ የሚጠናከርበትን እና የሚያድግበትን ስርዓት በመዘርጋት ድጋፍና ክትትል ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 6.ፌዴሬሽኑ በየክልሉ የሚካሄዱ የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶችን በየዓመቱ ክትትልና ግምገማ በማድረግ የግብረ መልስ ሪፖርት የሚላክበትን ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል: |
| | 7.ፌዴሬሽኑ በእድሜ ክልል (15፣17፣19፣21 እና 23) የአገር ውስጥ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች | የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| | ውድድሮችን ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 8.ፌዴሬሽኑ ዓለም አቀፍ የእግር ኳስ ማህበር (FIFA) በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች በእድሜ ክልል (15፣17፣19፣21 እና 23) ሀገሪቱን ወክለው የሚጫወቱ ወጣቶችን ሊያሳትፍ ይገባል፡፡ |
| | 9. ታዳጊ ሰልጣኞች ከሥልጠናው ጋር በተያያዘ ለሚያጋጥማቸው ጉዳት የህክምና አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 10. የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዳ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 11. ፌዴሬሽኑ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካትና የተሻለ የፋይናንስ ቁጥጥር ስርዓት እንዲኖር የሚያስችል የውስጥ ኦዲት ክፍል ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| 2. በሀገሪቱ የእግር ኳስ ስፖርትን ለመምራትና ለማስተዳደር ቀልጣፋና ውጤታማ የሥልጠናና የውድድር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መሆኑን ማጣራት፣ | 12. ፌዴሬሽኑ ስትራቴጂክ እቅድ በመንደፍ በእቅዱ የተገለፁ ተግባራት ወደ አመታዊ እቅድ ተመንዝሮ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 13. ፌዴሬሽኑ የእቅድ አፈፃፀሙን የሩብ ዓመቱና በአመቱ መጨረሻ ሊገመግም ይገባል፡፡ |
| | 14. ፌዴሬሽኑ በሚዘጋጀው አመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ውስጥ አፈፃፀም ላይ የታዩ ክፍተቶች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ማካተት አለበት፡፡ |
| | 15. ማንኛውም ክለብ ሲቋቋም የአፍሪካ እግር ኳስ ማኅበር (CAF) እና የዓለም አቀፍ እግር ኳስ ማኅበር (FIFA) ደረጃ የካፍ ላይሰንስና የፊፋ ስታተስ የሚጠይቀውን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት አለበት፡፡ |
| | 16. የአፍሪካ እግር ኳስ እና የዓለም አቀፍ እግር ኳስ ማኅበር ያስቀመጡትን ቅድመ-ሁኔታዎች በማሟላት የተቋቋሙ ክለቦች በየዓመቱ የገቢና ወጪ ሂሳባቸውን በውጭ ኦዲተር |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች | የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| | ማስመርመራቸውን ፌዴሬሽኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 17. ፌዴሬሽኑ በራሱ ገቢ ለማስተዳደር የሚያግዘውን የገቢ ማሰባሰቢያ ስልት ነድፎ ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡ |
| | 18. ፌዴሬሽኑ ብሄራዊ ቡድኑን የሚያሰለጥኑ አሠልጣኞችን ለመምረጥ የሚያስችል ግልፅ የሆነ የመመልመያ መስፈርት አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 19. ፌዴሬሽኑ የእግር ኳስ ክለቦችን እና ተጨዋቾችን ለማበረታታትና እውቅና ለመስጠት የሚያስችል ግልፅና ወጥ የሆነ የሽልማት አሰጣጥ መመሪያ ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 20. ፌዴሬሽኑ ከእግር ኳስ ስፖርት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክሶችና አቤቱታዎችን በማጣራት በመተዳደሪያ ደንቡና በዲሲፕሊን መመሪያው መሰረት ውሳኔ በመስጠት መረጃዎችን ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| | 21. ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው የአገር ውስጥ ውድድሮች እንዲሁም በሁሉም ክልሎች እና የከተማ መስተዳድሮች ላይ የፀረ-ዶፒንግ /አበረታች መድሐኒቶች/ኮንቬንሽን ተግባራዊ የሚደረግበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊነቱን መከታተል አለበት፡፡ |
| | 22. ፌዴሬሽኑ ተተኪ ስፖርተኞችን ለማፍራት የሚያስችል የምልመላና የሥልጠና ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 23. ፌደሬሽኑ የአሰልጣኝነትና የዳኝነት ስልጠና ኮርስ የሚሰጡ አሰልጣኞች እና ስልጠናውን የሚወስዱ ተሳታፊዎችን ለመምረጥ የሚያስችል ግልፅ የመምረጫ መስፈርት/መመሪያ አዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 24. ፌዴሬሽኑ የሚያዘጋጃቸው በሁሉም ሊጎች የአገር አቀፍ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች | የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| | ውድድሮች የፊፋን የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በማድረግ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 25. በሁሉም ሊጎች የሚደረጉ ውድድሮች በወጣው ፕሮግራም መሰረት ሊካሄዱ ይገባል፡፡ |
| | 26. ፌዴሬሽኑ በየውድድር ዓመቱ የሚያወጣቸው የሁሉም ሊጎች የውድድር መርሐ-ግብሮች የሁሉንም ክለቦች ፍላጎት (የውድድር ቦታ፣ ሰዓት፣ወዘተ) ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ |
| | 27. ፌዴሬሽኑ የአለም አቀፍ ደረጃን የጠበቁ የእግር ኳስ ማሰልጠኛ ማዕከላት ተገንብተው በአስፈላጊው የሰው ሃይልና ቁሳቁስ ተሟልተው ስራ እንዲጀምሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 28. ፌዴሬሽኑ የአሰልጣኝነትና የዳኝነት ስልጠና ለመስጠት መርሐ-ግብር ከማውጣቱ በፊት የክልሎችና የክለቦችን የስልጠና ፍላጎት (የስልጠናው ይዘት፣ የሚወስደው የጊዜ መጠን ፣ የትምህርት ዝግጅት ወዘተ) ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡ |
| | 29. ለአሰልጣኝነትም ሆነ ለዳኝነት ስልጠና የሚሰጡ እና ፈተናዎችን የሚያዘጋጅ (የሚፈትን) የተለያዩ ገለልተኛ አካላት /ባለሙያ/ ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 30. ብሔራዊ ቡድኑ ለሚኖረው የነጥብ ጨዋታ የወዳጅነት (የአቋም መለኪያ) ጨዋታዎችን የሚያከናውንበትን ሁኔታዎች ሊያመቻች ይገባል፡፡ |
| | 31. ሀገርን ወክለው በተለያየ ደረጃ ለሚወዳደሩ ብሔራዊ ቡድኖች አባላት ለልምምድ ሆነ ለውድድር የሚያስፈልጋቸው ቁሳቁሶች እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ግብዓቶች ሊያሟላ ይገባዋል፡፡ |
| | 32. ፌዴሬሽኑ የአሠልጣኞችና የዳኞችን ደረጃ የሚያረጋግጥ መስፈርት ሊያዘጋጅ፣የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች | የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| | 33. ፌዴሬሽኑ በክለቦች መካከል የሚደረግ የአማተር፣ የፕሮፌሽናልና የውጭ አገር ተጫዋቾች ዝውውር ሂደት በመመሪያው ላይ የተቀመጡ መስፈርቶች መሟላታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| 3. .በፌዴሬሽኑ የእግር ኳስ ስፖርትን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ አጠባበቅ፣ አጠቃቀምና ልውውጥ አጥጋቢ እና አስተማማኝ መሆኑን መገምገም፣ | 34. ፌዴሬሽኑ የእግር ኳስ ልማትን ለማሳደግ የተለያዩ የመገኛኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 35. ፌዴሬሽኑ ለስፖርት ኮሚሽን ዓመታዊ እቅዱንና የየሩብ ዓመትና የዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡ |
| | 36. ፌደሬሽኑ ከክፍለ-አህጉር፣ ከአህጉርና ዓለም አቀፍ የእግር ኳስ ማህበራት ጋር ያለውን የመረጃ ልውውጥ ሊያጠናክር ይገባል፡፡ |
| | 37. ፌዴሬሽኑ እግር ኳስ ስፖርትን የሚመለከቱ መረጃዎች በዘመናዊ መልክ ተጠናቅረው የሚያዙበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 38. ፌዴሬሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎች የተለያዩ ተጠቃሚ ወገኖች የሚያገኙበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 39. የሀገሪቱን የእግር ኳስ ስፖርት ሁኔታ የሚመለከት ወቅታዊ መረጃ ለተጠቃሚዎች በመረጃ መረብ፣ በመጽሔትና በበራሪ ወረቀቶች ሊያሰራጭ እንዲሁም የፌዴሬሽኑ የመረጃ መረብም በየቀኑ ወቅታዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 40. ፌዴሬሽኑ በህፃናት እግር ኳስ ልማት ዙሪያ ከጋራ ትብብር ኮሚቴው (ከጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ ከትምህርት ሚ/ር፣ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከስፖርት ኮሚሽን) ጋር በጋራ ለመስራት በተፈራረሙት ሰነድ መሰረት እቅድ በማቀድ ተግባራዊ እንዲሆን በጋራ ሊንቀሳቀሱ ይገባል፡፡ |
| | 41. ፌዴሬሽኑ ለሚያሰራቸው ማንኛውም የግንባታ ፕሮጀክቶች |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች | የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች */Evaluative Criteria/* |
|---|---|
| | በጨረታ ሕጉ መሰረት ኮንትራክተሮችን ሊመርጥ ይገባል፡፡ |
| | 42. ፌደሬሽኑ ከፊፋ (አለም አቀፍ የእግር ኳስ ማህበር) ለቴክኒካል ዕርዳታ የሚላከውን የማቴሪያል እርዳታዎችን በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ ለዓለም አቀፍ እግር ኳስ ማህበሩና ለስፖርት ኮሚሽን ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 43. ፌዴሬሽኑ ከፊፋ የሚላከውን የስታዲየምና የቢሮ የግንባታ ማስፈፀሚያ በጀት በወቅቱ ጥቅም ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 44. ፌዴሬሽኑ የስታዲየምና የቢሮ ግንባታ አፈፃፀምን በተመለከተ ለፊፋ ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡ |

# አባሪ 3፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ ባለድርሻ አካላት ዝርዝር

| ተራ ቁጥር | የታዩ ቢሮዎች፣ ፌዴሬሽኖች፣ ክለቦችና ፕሮጀክቶችዝርዝር |
|---|---|
| 1. | <u>**በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት**</u><br>- የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ<br>- የእግር ኳስ ፌዴሬሽን<br>- የዳኞች ማህበር<br>- የአሰልጣኞች ማህበር<br>- መቀሌ ከተማ እና ወልዋሎ ክለቦች<br>- ከ15 ዓመት በታች የእድሜ ክልል የታቀፉ ፕሮጀክቶች ከያንዳንዳቸው በሁለቱም ጾታዎች አንድ አንድ ፕሮጀክቶች<br>- አንድ የህፃናት ልማት ፕሮጀክት |
| 2. | <u>**በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት**</u><br>- ሰበታ ከነማና ቡራዩ ከነማ እና ክለቦች<br>- ከ15 ዓመት በታች የእድሜ ክልል የታቀፉ ፕሮጀክቶች ከያንዳንዳቸው በሁለቱም ጾታዎች አንድ አንድ ፕሮጀክቶች<br>- አንድ የህፃናት ልማት ፕሮጀክት |
| 3. | <u>**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፡-**</u><br>- የእግር ኳስ ፌዴሬሽን<br>- የቅዱስ ጊዮርጊስ እና የኢትዮጵያ ቡና ክለቦች<br>- ከ15 ዓመት በታች የእድሜ ክልል የታቀፉ ፕሮጀክቶች ከያንዳንዳቸው በሁለቱም ጾታዎች አንድ አንድ ፕሮጀክቶች<br>- አንድ የህፃናት ልማት ፕሮጀክት |